ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 216 ሚያዝያ 6 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## ልዩ ኃይሎችን እንደገና የማደራጀቱ ፋይዳ



**ፋንታነሽ ክንዴ**

ባለፉት ጊዜያት እንደሀገር መፍትሔ ያስፈልጋቸዋል ተብለው ከሚነሱት ጉዳዮች መካከል የክልል ልዩ ኃይሎች አደረጃጀት አንዱ ነበር። ከሰሞኑ መንግሥት የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ ለማደራጀት የጀመረው እንቅስቃሴ የብዙዎች አጀንዳ ሆኖ ሰንብቷል።

የክልል ልዩ ኃይሎች እንደገና መደራጀት ላይ ብዙ ኢትዮጵያውያን ቢስማሙም ለምን በዚህ ጊዜ የሚል ጥያቄ ጎላ ብሎ ተስተጋብቷል። ከዚህም በተጨማሪ መልሶ ግንባታው የአንድ ክልል ልዩ ኃይልን ለማፍረስ ያለመ ነው የሚል ሀሳብም ሲንሸራሸር ተስተውሏል። ከዚህ ጋር በተያያዘም አንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሰላም መደፍረስ ተከስቷል።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ የመንግሥት

ልዩ ኃይሎችን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## «ማዕድ የምናጋራው ለዜጎች ያለንን ክብር ለመግለጽ ነው»

- የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ለአቅመ ደካሞች እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ማዕድ የምናጋራው ለዜጎች ያለንን ክብር ለመግለጽ ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አበቤ የትንሳዔና የኢድ አልፈጥር በዓልን ምክንያት በማድረግ ለአቅመ ደካሞች እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ማዕድ አጋርተዋል። በተጨማሪ ዝቅተኛ የኑሮ

«ማዕድ የምናጋራው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

## የካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ የኢፕድን የካበተ ልምድ በመጠቀም የተደራጀ መረጃ እንዲኖረው ይሠራል

- ሆስፒታሉ በ100ኛ ዓመት ክብረ በዓሉ ዙሪያ ከኢፕድ ጋር በጋራ ለመሥራት ስምምነት ተፈራርሟል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የኢፕድን የካበተ የታሪክ ስነዳ ልምድ በመጠቀም የተደራጀ መረጃ እንዲኖረው ለማስቻል እንደሚሠራ የየካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ አስታወቀ። የካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ የ100ኛ ዓመት ክብረ በዓሉን ከኢፕድ ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችለውን ስምምነት ተፈራርሟል።

የየካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ምክትል "ፕሮቮኮስት" አቶ ዓለሙ ክብረት በስምምነቱ ወቅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሚዲያው ዘርፍ ረጅም እድሜ ያስቆጠረ አንጋፋ ተቋም ነው። በረጅም ጊዜው ሰፋ ያሉ የዘገባ ሥራዎችን በመሥራት

የካቲት 12 ሆስፒታል ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል

## «የጤፍ አቅርቦቱ በቂ ባይሆንም እየተሻሻለ ነው»

- የከተማዋ የኅብረት ሥራ ማኅበራት

## «ከበዓል ጋር ተያይዞ የአቅርቦት እጥረት እንዳይኖር እየሠራሁ ነው»

- የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ



ገጽ 4



# ጥራትና ደህንነታቸው ያልተረጋገጡ ምርቶች ሲገኙ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ ይገባል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በበዓላት ግብይት ወቅት ኅብረተሰቡ ጥራትና ደህንነታቸው ያልተረጋገጡ ምርቶችን ሲያገኝ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ እንዳለበት የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን አሳሰበ።

በባለሥልጣኑ የምግብ ተቋማት ቁጥጥር ዳይሬክተር አቶ በትረ ጌታሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከባዕድ ነገር ጋር የተቀላቀሉ፣ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈና አጠራጣሪ ነገር የሚታይባቸው ምርቶች ሲገኙ ለሕግና ቁጥጥር አካላት ማሳወቅ ያስፈልጋል።


በባለሥልጣኑ ፍቃድ የሌላቸው፣ ጥራትና ደህንነታቸው ያልተረጋገጡ ምግቦች በተለያዩ መንገዶች እየገቡ መሆኑን ኅብረተሰቡ በሚሰጠው ጥቆማ ማወቅ ተችሏል ብለዋል።

በተለይ በበዓላት ወቅት የግብዓት ፍላጎቶች ይጨምራሉ ያሉት አቶ በትረ ይህንን ክፍተት በመጠቀም የተወሰኑ ነጋዴዎች ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ቅቤ፣ ማር፣ በርበሬና የመሳሰሉ ምርቶች ላይ የተለያየ ባዕድ ነገር በመቀላል ለኅብረተሰቡ እንደሚሸጡ ገልጸዋል።

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ለተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከምግብ ደህንነት ጋር በተገናኘ መደረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መሠራቱን አቶ በትረ ተናግረዋል።

እንደ አቶ በትረ ገለጻ፤ በሀገር ደረጃ ያለው የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም በምግብ ምርቶች ግብይት ላይ ሕገ ወጦች እንዲበራከቱ ምክንያት ይሆናል። ኅብረተሰቡም ሕጋዊ ፍቃድ ከሌላቸው የንግድ ተቋሟት ምርቶችን ከመግዛት መቆጠብ ይኖርበታል።

ከዋጋ ቅናሽ ይልቅ ጥራት ላይ ትኩረት በማድረግ ጤናን ከሚጎዱ ምርቶች መጠበቅ ያስፈልጋል ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል።




ኅብረተሰቡ በዓላትን ምክንያት በማድረግ ማጭበርበር፣ያልተገባ ጥቅም ማግኘትና አጋጣሚውን ተጠቅመው መበልጸግ የሚፈልጉ አካላትን በማጋለጥ እራሱንና ማኅበረሰቡን ከሚጎዱ ተግባራት መጠበቅ እንዳለበትም ተናግረዋል።

አቶ በትረ እንዳስታወቁት፤ ማኅበረሰቡ ግብይት በሚፈጽምበት ወቅት የሚያጠራጥሩ ነገሮችን ሲመለከት በአጭር የጽሑፍ መልዕክት 8482 ለባሥልጣኑ ወይንም በአቅራቢያው ለሚገኝ የመንግሥት አካል ማሳወቅ ይኖርበታል።


አቶ በትረ ጌታሁን

# የካቲት 12 ሆስፒታል...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ታሪክ እየሰነደ የቆየ ሚዲያ ነው።

አሁን ያለንበት ዘመን ከሚዲያ ጋር ተያይዞ ሰፋ ያሉ ሥራዎች የሚሠሩበት ነው ያሉት አቶ ዓለሙ፤ ያለ ሚዲያ ሥራን መሥራት አስቸጋሪ የሆነበት ዘመን ስለሆነ የየካቲት 12 ሆስፒታል ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በተናጠል ሥራ ከመገናኘት ባሻገር ፕሬስ ያካበተውን ታሪክን የመሰነድ ልምድ በመጠቀም የሆስፒታሉ 100ኛ ዓመት ሲከበር ታሪኩን በሚገባ በመሰነድ በአግባቡ ለማኅበረሰቡ ለማስቀመጥ በጋራ ለመሥራት ዝግጁ መሆናቸው ገልጸዋል።

የካቲት 12 ሆስፒታል፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመጀመሪያው ኤክስሬይ ማሽን የገባበት፤ የመጀመሪያው የካንሰር ሕክምና የተጀመረበትና የመጀመሪያው የደም አገልግሎት የተሰጠበት የሕክምና ተቋም ነው ያሉት አቶ ዓለሙ፤ ጤና የማይመለከተው የማኅበረሰብ ክፍል የሌለ በመሆኑ በጤናው ዘርፍ የየካቲት ሆስፒታል 39 የሕክምና ዘርፎችና ሌሎች የትምህርት ዘርፎች ላይ በትኩረት እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሚፈልገው የትምህርት ነክም ሆነ የጤና ዘርፍ ላይ ሆስፒታሉ በጋራ ለመሥራት ቁርጠኛ ነውም ብለዋል።

አቶ ዓለሙ እንደገለጹት፤ ሆስፒታሉ 100ኛ ዓመቱን ለማክበር ሥራ ሲጀምር በሕክምናው ዘርፍ ረጅም ዕድሜ እንደ አስቆጠረ ተቋም ታሪኩ በአግባቡ አልተሰነደም። ስለሆነም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትን ታሪክ የመሰነድ የካበተ ልምድ በመጠቀም ሆስፒታሉን የሚመጠን ታሪክ ለመሰነድ የመግባቢያ ሰነድ መፈራረሙ ትልቅ እድል ነው።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሰ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሕትመት ሚዲያው የ82 ዓመት ዕድሜ ያለው ተቋም ነው። ስለሆነም በ18 ዓመት ዕድሜ ከሚበልጠው የሕክምና ተቋም ጋር መሥራት ትልቅ አጋጣሚና ዕድል ነው ብለዋል።

ሁለቱ ተቋማት በኢትዮጵያ የዘመናዊ ተቋማት ግንባታ ታሪክ ሂደት ውስጥ በወቅቱ የነበሩ መሪዎች ከራሳቸው ኪስ እያወጡ ያቋቋሟቸው ተቋማት መሆናቸውን የጠቆሙት አቶ ጌትነት፤ አዳዲስ ተቋማት ሊመሠረቱ፣ ሊፈርሱ፣ ከፊሎቹ ሊቀየሩ፣ አንዳንዶችም ሊያድጉ፣ ሊቀየሩ፣ እንዲሁም ሊዋሐዱ ይችላሉ። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትና



የየካቲት 12 ሆስፒታል ግን በነበሩበት መቀጠላቸው በራሱ የሚያስተላልፉት መልዕክት ትልቅ ነው ብለዋል።


እንደ አቶ ጌትነት ገለጻ፤ ተቋማት ባስቆጠሯቸው ዕድሜ ውስጥ የሚያከናውኗቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች እንዴት እንደተጀመሩ፤ ምን ውጤት እንዳስገኙ፤ ምን እንዳከናወኑ በአግባቡ ሰንዶ በመያዝ ረገድ እንደ ሀገር በርካታ ክፍተቶች አሉ። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አንዱ ሥራ በጋራ አብረውት ከሚሠሩ ተቋማት ጋር እያከናወነ ያለው ተቋማት ማንነታቸውን፣ ራሳቸውን፣ ተልዕኳቸውን፤ አበርክቷቸውንና ውጤቶቻቸውን በአግባቡ እየሰነዱ መያዝ እንዳለባቸው ትልቅ የሆነ ሀገራዊ ተነሳሽነት ወስዶ እየሠራ ነው።

ተቋማት የ25፣50፤ 60፤ 80ና እና የ100 ዓመት የምስረታ በዓላቸውን እንደሚያከብሩ የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ከማክበር ባሻገር ግን ተገቢውን የኮሙዩኒኬሽን ሥራ ሳይሠሩ ያሳለፉ ተቋማት አሉ። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የ80 ዓመቱን ሲያከብር ዕለታዊ ዜና እየዘገበ ታሪክን በአግባቡ መሰነዱን በተጨባጭ የተግባቡበት ሥራ በመሥራት ማሳየት ችሏል ብለዋል።

ስለዚህ የየካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ 100ኛ ዓመቱን ሲያከብር አገልግሎት የሚሰጠው ማኅበረሰብ በትክክል እንዲገነዘበው ትክክለኛ የኮሙኒኬሽን ሥራ መሥራት አስፈላጊ ነው። ኢፕድም ልምዱን በመጠቀም የሆስፒታሉ 100ኛ ዓመት ሌሎች ተቋማት ልምድ የሚወስዱበት ታሪክ እንዲሰነድ ለማድረግ ከሆስፒታሉ ጋር በትብብር ይሠራል ነው ያሉት።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ታሪክ መሰነድ ብቻ ሳይሆን የጥናትና ምርምር ሥራ በመሥራት ክፍተቶችን በመለየት አገር አቀፍ ሥልጠና በሚሰጥበት የሥልጠና ማዕከሉ በጥናትና ምርምርና በአቅም ግንባታ ታሪክን የመሰነድ ሥራው ተደራጅቶ እንዲሄድ ለማድረግ በትኩረት እየሠራ ነው ያሉት አቶ ጌትነት፤ ከሆስፒታሉ ጋር የተደረገውን የሁለትዮሽ የመግባቢያ ስምምነት እንደ ትልቅ አጋጣሚ በመጠቀም ለሌሎች ተቋማት ትምህርት በሚሰጥ መልኩ በጋራ ለመሥራት ላቅ ያለ ፍላጎት አለው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከዚህ በፊት ከበርካታ ተቋማት ጋር በጋራ ለመሥራት የስምምነት ሰነድ መፈራረሙ ይታወሳል።


ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ
ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ

# የሐጅ ጉዞ አገልግሎት ተዓማኒና ከእንግልት ነፃ በሆነ መልኩ ይከናወናል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡-የዘንድሮ የሐጅ ጉዞ መስተንግዶና ምዝገባ አገልግሎት ተዓማኒና ከእንግልት ነፃ በሆነ መልኩ እንደሚከናወን የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት አስታወቀ።

ለ1 ሺህ 444ኛው የሐጅ ጉዞ መስተንግዶ ማብራሪያና የአዲሱ የሐጅ ምዝገባ ሥርዓት ማስጀመሪያ መርሐ ግብር ትናንትና ተካሂዷል።

በወቅቱ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ እንደገለጹት፤ የዘንድሮውን የሐጅ መስተንግዶና ምዝገባ አገልግሎቱ ካለምንም እንግልት ማግኘት እንዲቻል ጥረት ይደረጋል።

የሐጅ ጉዞ ማካሄድ ከእስልምና መሠረቶች ውስጥ አንዱ ተግባር ነው ያሉት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም፤ የዘንድሮው 1 ሺህ 444ኛው የሐጅ ጉዞ ምዝገባ ሥርዓት በይፋ ተጀምሯል፤ አገልግሎቱ በተደራጀ አግባብ ይሰጣል ብለዋል።

ለአዲሱ የሐጅ ምዝገባ ሥርዓት መሳካት ሥራው የመጅሊሱ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ባለድርሻ አካላት ቅንጅት ይፈልጋል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤በተለይ ባንኮች በአብሮነት ከጎናቸው እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል።

የጠቅላይ ምክር ቤቱ የሐጅ ምዝገባ ሥርዓት ዋና ተጠሪ ኢንጂነር አንዋር ሙስጠፋ በበኩላቸው፤በአዲስ መልክ የተጀመረው የሐጅ ምዝገባ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊና ቀልጣፋ አገልግሎት ለማቅረብ የሚረዳ ነው ብለዋል።

ባለፉት ጊዜያት የሐጅ ምዝገባው በአዲስ አበባ ብቻ ይካሄድ የነበረ ሲሆን አሁን ከምዝገባው ጋር ተያይዞ የሚባክነውን ጊዜና ጉልበት ለመቀነስ በተለያዩ ከተሞች 16 የምዝገባ ጣቢያዎች መዘጋጀታቸውን አስታውቀዋል።

የዘንድሮው የሐጅ ጉዞ የክፍያ ሥርዓት ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ ከዘጠኝ ባንኮች ጋር በትብብር የሚሠራበት የክፍያ አማራጭ መዘጋጀቱንም አስረድተዋል።

ባለፉት ጊዜያት የነበረው የሐጅ መስተንግዶ ችግሮች የነበሩበት ነው ያሉት ኢንጂነር አንዋር፤ በአዲስ መልኩ የተጀመረው ምዝገባ አለአግባብ የሆኑ አሠራሮችና እንግልትን የሚያስቀር መሆኑን ጠቁመዋል።

በማስጀመሪያ መርሐ ግብሩ ወቅት አሠራሩን ቀልጣፋ ለማድረግ ሐጅ ማኔጅመንት ሲስተም ድረ-ገጽ ይፋ የተደረገ ሲሆን፤ ወረቀት አልባና አማራጭ የክፍያ ሥርዓቶችን ያካተተ እንዲሁም ሐጃጆች ባሉበት ሆነው አገልግሎቱን እንዲያገኙ የሚያስችል መሆኑ ተመላክቷል።

በ1 ሺህ 443ኛው የሐጅ መስተንግዶ በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ከስምንት ሺህ በላይ የሐጅ ተጓዦች ከጉዞው መቅረታቸው የገለጸው ምክር ቤቱ፤ ችግሩን ለመቅረፍ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ጋር በትብብር በመሥራቱ ዘንድሮ መፍትሔ ማምጣት እንደተቻለ ገልጿል።

የ2015 ዓ.ም አጠቃላይ የሐጅ መስተንግዶ ዋጋ 315 ሺህ ብር መሆኑን ጠቅላይ ምክር ቤቱ አስታውቋል።

የውጭ ምንዛሪ መጨመር፣የመዳረሻ ቦታዎች ክፍያ መጨመር፣ ለዘመናዊው የሐጅ ምዝገባ ሥርዓት አስተዳደራዊ ወጪ መጠየቁ እንዲሁም የተጓዥን ምቾት ለመጠበቅ ሲባል ዘመናዊ ማረፊያ ሆቴሎች ኪራይ መያዛቸው የ2015 የሐጅ መስተንግዶ ዋጋ እንዲጨምር ካደረጉ ምክንያቶች መካከል መሆናቸውም ተጠቁሟል።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN MEDIA AUTHORITY

## የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃን የሚያሰራጩ አጥፊዎች በሕግ እንዲጠየቁ እየተሠራ ነው

**በዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃ የሚያሰራጩ አካላት በሕግ እንዲጠየቁ እየሠራሁ ነው ሲል የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን ገለጸ። መገናኛ ብዙኃን የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃን በማሰራጨት ሕዝብን ከሚከፋፍል ተግባር በመቆጠብ ለሀገር ብሔራዊ ጥቅም የበኩላቸውን መወጣት ይኖርባቸዋልም ብሏል።

የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ደሴ ከፋለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሕዝቡን አብሮነት የሚሸረሽሩና ግጭት በሚያባብሱ የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃን የሚያሰራጩ አካላት ላይ ከሕዝቡ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን መሠረት አድርጎ አስፈላጊውን መረጃ በማጣራት አጥፊዎች በሕግ እንዲጠየቁ ለሚመለከታቸው አካላት መረጃውን ተደራሽ እያደረገ ይገኛል።

እንደ አቶ ደሴ ገለጻ፤ በሕጉ መሠረት የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃን ያሰራጨ አካል በወንጀል ነው የሚጠየቀው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ኅብረተሰቡ የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃን በመገናኛ ብዙኃንና በማኅበራዊ ሚዲያ በሚመለከትበት ጊዜ ለባለስልጣኑ እንዲጠቁም 9192 ነፃ የስልክ መስመር ተዘርግቷል።

የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃ በማሠራጨት የዜጎችን አብሮነት እየሸረሸሩ እና የሀገርን ሰላም አደጋ ላይ እየጣሉ ስለ ብሔራዊ ጥቅም ማውራት ዋጋ የለውም ያሉት አቶ ደሴ፤ የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃ ሀገርን አንድነትን አደጋ ላይ በመጣል የብሔራዊ ጥቅማችንን የሚጎዳ ተግባር በመሆኑ ሁሉም ዜጋ ሊከላከለው ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ሀገራት ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስከበር መገናኛ ብዙኃኖቻቸውን ይጠቀማሉ ያሉት አቶ ደሴ፤ የሀገራችን መገናኛ ብዙኃን ዘብ ሊቆሙለት ከሚገባቸው ብሔራዊ ጥቅሞቻችን መካከል አንዱ የሀገር አንድነትን እና የዜጎች ወንድማማችነትን ማስጠበቅ ነውም ብለዋል።

አቶ ደሴ መገናኛ ብዙኃን የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃን በማሰራጨት ሕዝብን ከሚከፋፍል ተግባር በመቆጠብ ለሀገር ብሔራዊ ጥቅም የበኩላቸውን መወጣት ይኖርባቸዋልም ብለዋል።

ባለሥልጣኑ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃን በተመለከተ የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ሊያሳድጉ የሚችሉ መልዕክቶችን በመቅረፅ በባለሥልጣኑ ማኅበራዊ ሚዲያ ገፆችና በመገናኛ ብዙኃን በማስተላለፍ በሕግ የተጣለበትን ኃላፊነት እየተወጣ ይገኛል።

የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ 1185/12 በዋናነት የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ለማኅበራዊ ግንኙነት፣ ለፖለቲካ መረጋጋት፣ ለሃገራዊ አንድነት፣ ለሰብዓዊ ክብር፣ ለብዝኃነትና ለእኩልነት ጠንቅ በመሆን ሆን ተብሎ የሚሰራጩ የጥላቻና ሐሰተኛ ንግግሮችን በሕግ መከልከልና መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ መሆኑንም አቶ ደሴ ገልጸዋል።

# «የትኛውም ዓይነት በደል በመስቀል ከተከፈለው ዋጋ ስለማይበልጥ ይቅር ተባብሎ ወደፊት መሄድ ያስፈልጋል»

*- መጋቢ ቸርነት በላይ*

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የትኛውም ዓይነት በደል ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ላይ ሆኖ ለሰው ልጆች ከከፈለው የሕይወት ዋጋ አይበልጥምና ይቅር ተባብሎ ወደፊት መሄድ ያስፈልጋል ሲሉ መጋቢ ቸርነት በላይ ገለጹ። ፓስተር ቸርነት ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች ለኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለትና ትንሳኤ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።



መጋቢ ቸርነት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት እንደተናገሩት፤ እስከ ሕይወት ድረስ በተከፈለበት የመስቀሉ መስዋዕትነት ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ዘር ሁሉ ከከፈለው ዋጋ በላይ መበደል የደረሰበት ሰው የለምና ይቅር ተባብሎ ወደፊት መሄድ ያስፈልጋል።

ሰሞነ ሕማማት ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ሕዝብን ለማዳን እንዲሁም የሰው ልጆችን እዳ ለመክፈል ከሰማያት ወርዶ ስቃይን ያየበት እና የሰው ልጆችን ሕመም የተሸከመበት እንዲሁም ወድቆ የተነሳበት በመሆኑ ይህ ወቅት ሁላችንም በምን እንደዳንን ጥሞና የምንይዝበት ነው ሲሉም ገልጸዋል።

ወቅቱ የክርስቶስን ሕማም የምናስብበት በመሆኑ ኢየሱስ እንዲህ ባይሰቃይ እኔ በሕይወት መኖር አልችልም የሚል ክርስቲያን ሁሉ ኢየሱስ እንደዚህ ተገርፎ ተገፍቶ ይቅር ካለ እኛም ምድራዊውን በደል ይቅር የምንልበት አቅም ልናገኝ ይገባል ሲሉም መጋቢ ቸርነት ገልጸዋል።

እንደ መጋቢ ቸርነት ንግግር፤ “እኔ ይቅርታ ላደርግ አልችልም፣ እኔ የተበደልኩት በደል ብዙ ነው” የሚሉ ሰዎች አሉ፤ ነገር ግን የነሱ በደል ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከደረሰበት በላይ አይደለምና መበዳደል ውስጥ ያለ ሁሉ ይቅር ሊባባል ይገባል።

የክርስቶስ መስዋዕትነት መበደልን በይቅርታ ማለፍ የሚያስችል አቅምን ይሰጣል ያሉት መጋቢ ቸርነት፤ በመሆኑም ሁሉም አማኝ በደሉ ከተከፈለለት ውድ የሕይወት ዋጋ አለመብለጡን በማሰብ በቤተሰብ፣ በጎረቤት፣ በክልልም ሆነ በሀገር ደረጃ ይቅር መባባል እንደሚያስፈልግ ነው የተናገሩት።

ሰሞኑን በጥሞና ሊያስብ የሚሻ በሙሉ የኢየሱስ ክርስቶስን አርዓያነት መከተል አለበት ያሉት መጋቢ ቸርነት፤ ፍቅርን ቢላበስ ሊስብ ይቅርታ ቢደራረግ ምህረት ቢሰጣጥ መልካም መሆኑን ተናግረዋል።

ኢየሱስ እኛን እስከ ሞት ድረስ የወደደን ምሕረት የሚያሰጥ ምክንያት ተገኝቶብን አይደለም ያሉት መጋቢ ቸርነት፤ ከፍቅር የተነሳ ዋጋ እንደተከፈለልን አስበን ይህን በዓል ይመለከተኛል የሚል ሁሉ አጠገቡ ያለውን ሰው በፍቅር ተሞልቶ ይቅርታ ቢያደርግለት መልካም መሆኑን ተናግረዋል።

ክርስቲያኖች አምላካቸው እግዚአብሄር አንድያ ልጁን በመስጠት ምድርና መላውን ሕዝብ እንዳዳነ ሁሉ ክርስቲያን የተባለ ሁሉ ያለውን ያለምንም ንፍገት ለሌለው በመስጠት ቸር በመሆን መኖር እንደሚገባው ገልጸዋል።

ፓስተር ቸርነት ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች ለኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለትና ትንሳኤ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ለበዓሉ የሚቀርቡትን አገልግሎቶች በተደራጀ መንገድ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን ከተማ አስተዳደሩ አስታወቀ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ለትንሳኤ በዓል የሚቀርቡ የውሃ፣የኤሌክትሪክ፣ የእሳት አደጋና የቄራ አገልግሎቶች ሳይስተጓጎሉ ለነዋሪው በተደራጀ መንገድ ለማቅረብ ዝግጁ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዝግጁ መሆኑን አስታወቀ።

በቢሮ ኃላፊ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ታረቀኝ ወርቅነህ ትላንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ የከተማዋ ማዘጋጃ ቤት ለትንሳዔ በዓል ለሕዝቡ የሚያቀርባቸውን አገልግሎቶች በተደራጀ መንገድ ለማቅረብ ቅድመ ዝግጅት አድርጓል። አገልግሎቶቹን ጥራታቸውን ጠብቀው በተሟላ መንገድ ለሕዝቡ ለማቅረብም በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

ሥጋን በሰፊና በጥራት ለማቅረብ የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ሰፋ ያለ ዝግጅት ማድረጉን የጠቀሱት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ፤ የሥጋ አቅርቦትን ንጽሕና የመጠበቅ፣ጥገና የማድረግና በቂ የሥጋ ማቅረቢያ ተሽከርካሪዎችን የማሟላት ሥራዎችን ሲያከናውን መቆየቱን አንስተዋል። ከበዓሉ ዕለት ጀምሮ የ24 ሰዓት አገልግሎት እንደሚሰጥም አስታውቀዋል። ንጽሕናውና ጥራቱ የተረጋገጠ ሥጋ ለሕዝቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጓል ነው ያሉት።

በሌላ በኩል ለበዓል ተብሎ የተዘጋጀ ከ500 ሺህ በላይ የኅብረተሰብ ክፍል የሚሳተፍበት ሰፊ ባዛር መኖሩንም ገልጸዋል። በኤግዚቢሽን እንቅስቃሴው ሰፋፊ የኢንዱስትሪ ውጤቶች፣ አልባሳትና የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች አቅርቦቶች መኖራቸውን ጠቁመዋል። ኅብረተሰቡ እስከ በዓሉ ዋዜማ ድረስ መርጦ መግዛት የሚችልበት ሁኔታ መፈጠሩንም ተናግረዋል።

በበዓሉ ዋዜማ አብሮነትን መግለጽ የሚያስችል የሁሉም እምነት ተከታዮች በአንድነት የጽዳት አገልግሎት እንደሚያከናውኑም ገልጸዋል። በበዓል ማግስት የእርድ ውጤት የሆኑ ተረፈ ምርቶችን ለጤና እክል እንዳይፈጥሩ ኅብረተሰቡ በአንድ አካባቢ ላይ ሰብስቦ በየአካባቢው ለሚሠማሩ የሸርክና ማኅበራት እንዲሰጥም ምክትል ሥራ አስኪያጁ አሳስበዋል።



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

**ዶክተር ገበየሁ ሲካሳ፣ አቶ ታረቀኝ ወርቅነህ፣ ኮሚሽነር ፍስሐ ጋረደው**

በከተማዋ ያለው የውሃ ፍላጎትና አቅርቦት የተመጣጠነ ባለመሆኑ፤ ከአየር ፀባይ ለውጥና ከኤሌክትሪክ ጋር ተያይዞ መቆራረጥ እንደሚያጋጥም ጠቅሰዋል። ይህ በበዓሉ ወቅት እንዳያጋጥም ሰፊ ሥራዎች ይከናወናሉ ብለዋል። ችግር ቢከሰት ወዲያው ምላሽ የሚሠጡ ቡድኖች እንደተደራጁም ገልጸዋል።

የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽነር ፍስሐ ጋረደው በበኩላቸው፤ ኮሚሽኑ በበዓል ወቅትም ሆነ ከበዓል ውጪ በከተማዋ የሚከሰቱ አደጋዎችን የመቆጣጠርና ግንዛቤ የመስጠት ሥራዎችን እንደሚሠራ ጠቅሰው፤ የትንሳዔና ኢድ ዓል ፈጥር ሃይማኖታዊ በዓላትን ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ቅነሳና አደጋን የመቆጣጠር ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል።

አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ የከተማዋ ነዋሪዎች እንቅስቃሴያቸው በጥንቃቄ የተሞላ እንዲሆን ከሚያዝያ 2 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ በገበያ ስፍራዎች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥባቸውና ሕዝብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች የማስገንዘብ ሥራ መከናወኑን ተናግረዋል።

አደጋን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ መሣሪያዎችን ደኅንነት የመፈተሽና ዝግጁ የማድረግ ሥራ እንደተከናወነና፤ በዚህም ከ570 በላይ 24ቱንም ሰዓት በዝግጁነት የሚሠሩ ባለሙያዎች መኖራቸውን አስታውቀዋል። የቅድመ ሆስፒታል የአምቡላንስ አገልግሎትም ዝግጁ እንደሆነ ጠቅሰዋል። ኅብረተሰቡ የሚጠቀመው ኢነርጂ አደጋ የሚያስከትል እንዳይሆን ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግና አደጋ ሲያጋጥመውም 939 የጥሪ ማዕከልን በአግባቡ እንዲጠቀምና አሽከርካሪዎችም ጠጥቶ ከማሽከርከር አደጋ ራሳቸውን እንዲጠብቁ አሳስበዋል።

የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ገበየሁ ሊካሳ፤ በበዓላቱ ከፍተኛ የኃይል አጠቃቀም መኖሩን ጠቅሰዋል። አገልግሎቱም በበዓል ወቅት የኃይል መቆራረጥ እንዳያጋጥምና ካጋጠመም በአፋጣኝ ወደ አገልግሎት ማስገባት እንዲቻል ሰፊ የቅድመ ዝግጅት አድርገናል ብለዋል። ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ የተፈጠረውን የኃይል መቆራረጥ አዲስ ቡድን በማዋቀር ወደ አገልግሎት ማስገባት እንደተቻለ ጠቁመዋል። ተጨማሪ ሀብትና ግብዓት በመመደብ 24 ሰዓት የሚሠራ ቡድን በቅድመ ዝግጅቱ ወቅት መዋቀሩን ገልጸዋል።

ዜና

# «የጤፍ አቅርቦቱ በቂ ባይሆንም እየተሻሻለ ነው»

*- የከተማዋ የኅብረት ሥራ ማኅበራት*

# «ከበዓል ጋር ተያይዞ የአቅርቦት እጥረት እንዳይኖር እየሠራሁ ነው»

*- የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ*

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ የጤፍ አቅርቦቱ በቂ ባይሆንም እየተሻሻለ መሆኑን በአዲስ አበባ የሚገኙ የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች ገለጹ። የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በበኩሉ የጤፍ አቅርቦትን ለማሻሻል እየሠራሁ ነው ብሏል።

በንፋስ ስልክ ክፍለ ከተማ የንጋት ኅብረት ሥራ ዩኒየን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ገብሬ ተክሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ካለፈው ወር ጀምሮ ከተማ አስተዳደሩ በፈጠረው የገበያ ትስስር ከነጋዴዎችና ከዩኒየኖች የተገኘውን ጤፍ በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ እያቀረቡ ነው። ሆኖም ምርቱን ለኅብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀረብን ቢሆንም የአቅርቦት እጥረት አልተቀረፈም ብለዋል።

ኅብረተሰቡ በተደጋጋሚ ጤፍ ለመግዛት ሲመጣ በስፋት ባለማግኘቱ ስጋት ውስጥ ገብቷል ያሉት አቶ ገብሬ፤ የጤፍ አቅርቦት ችግር ከተፈታ በከተማዋ የሚስተዋለው አጠቃላይ የፍጆታ ምርቶች ችግር የሚፈታ ይሆናል። ችግሩንም ለመቅረፍ ከነጋዴዎች፣ ከዩኒየኖች እና ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በጋራ እየሠራን ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የምዕራብ ሸማቾች ኅብረት ሥራ ዩኒየን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ በላይ ቶሌራ በበኩላቸው፤ በከተማዋ ያለው የጤፍ አቅርቦት እየተሻሻለ ቢሆንም አቅርቦቱ ወጥ የሆነ አይደለም ብለዋል።

ይህም ኅብረተሰቡ የአቅርቦት ደረጃውን በመመልከት ሁለትና ሦስት ኩንታል የመግዛት ፍላጎት እንዲያድርበት ማድረጉን ገልጸዋል።

የኅብረት ሥራ ማኅበራት አንድ ኪሎ የጤፍ ዋጋ በተቻለ መጠን ከ60 እስከ 70 ብር እንዳይበልጥ እየሠሩ ነው ያሉት አቶ በላይ፤ በቂ የጤፍ አቅርቦት በኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚሰራጭ ከሆነ በከተማዋ የጤፍ ዋጋ ይቀንሳል ብለዋል።

በዓሉን በተመለከተም ከጤፍ በተጨማሪ የስንዴና የበቆሎ ዱቄት፣ መኮሮኒ፣ ፓስታ፣ ሩዝ እና ለእለት ተእለት የሚውሉ ምርቶች ለኅብረተሰቡ መቅረባቸውን ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ ቢኒያም ምክሩ በበኩላቸው፤ ቢሮው ካለፉት ሦስት ሳምንታት ጀምሮ ከኦሮሚያ ክልል የሰብል ምርቶችን በስፋት ወደከተማው እንዲገባ ሲያደርግ ቆይቷል። የገባውን የጤፍ ምርት በከተማዋ የሚገኙ የሸማቾች የህብረት ሥራ ማኅበራት እና ዩኒየኖች በኩል ለኅብረተሰቡ በተመጣጣኝ እያቀረበ ነው ብለዋል።

በተለይ ከበዓል ጋር ተያይዞ በከተማዋ የአቅርቦት እጥረት እንዳይኖር እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ቢኒያም፤ በዓሉን በማስመልከት ከኦሮሚያ ክልል ሁለት ሺህ 700 ኩንታል ጤፍ መረከባቸውንና ተጨማሪ ሦስት ሺህ ኩንታል ጤፍ ወደ አዲስ አበባ እየገባ መሆኑን አብራርተዋል።

ይህም በመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት እና ዩኒየኖች አማካኝነት ለሁሉም ክፍለ ከተሞች የሚከፋፈል ይሆናል ብለዋል።

ይህም ካለፉት ሳምንታት ጀምሮ ሲገባ ከነበረው ምርት ጋር ተዳምሮ በከተማዋ ያጋጠመውን የሰብል እጥረት ለመቅረፍ ጉልህ ሚና እንደሚኖረውም አቶ ቢኒያም ተናግረዋል።

# «ማዕድ የምናጋራው...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ደረጃ ላይ ለሚገኙና ድጋፍ ለሚሹ ከ550 በላይ የከተማዋ ነዋሪዎች የቤት እድሳት መደረጉንም ተናግረዋል።

ከንቲባዋ በማዕድ ማጋራት መርሐ ግብሩ እንደተናገሩት፤ ማዕድ ማጋራት አንድነትንና አብሮነትን በተግባር የምናሳይበት ሰውኛ ተግባር ነው። ሃይማኖታዊ በዓላት የመደጋገፍ እሴቶች መገለጫዎች በመሆናቸው በከተማዋ የትንሳዔና የኢድ አልፈጥር በዓልን ምክንያት በማድረግ ማዕድ ማጋራት ተካሂዷል። በዚህም ለ256 ሺህ ለሚሆኑ አቅመ ደካሞች፣ ለችግር ለተጋለጡ ዜጎች፣ ለአገር ባለውለታዎች እንዲሁም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ማዕድ ተጋርቷል።

ይህንን የምናደርገው የበጎነት እሴቶቻችን ዳብረውና ተጠናክረው ለትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ለከተማችን ነዋሪዎች ማዕድ ማጋራት እንድንችል አቅም ለሆናችሁን የከተማችን ባለሃብቶች፣ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሰጪዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በከተማ አስተዳደሩ ስም አመሰግናለሁ ብለዋል።

ከማዕድ ማጋራት በተጨማሪ የዜጎችን ሕይወት ሊያቀሉ የሚችሉ እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆኑን ጠቁመው፤ በበዓላት ከፍተኛ የዋጋ ንረት የሚኖር በመሆኑ ጫናው ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው የማኅበረሰቡ ክፍሎች ላይ እንደሚሆን ጠቅሰዋል።

በተለይ በበዓል ወቅት ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ዜጎች ላይ የሚደርሰውን ጫና ለመቀነስ በእሁድ ገበያ፣ በሸማቾችና በሌሎች አማራጮች ምርት ወደከተማዋ እንዲገባ እና በተመጣጣኝ ዋጋ ነዋሪዎች እንዲያገኙ እየሠራን ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ይህ ሥራ እንደተጠበቀ ሆኖ በተመጣጣኝ ዋጋም ቢሆን መሸመት የማይችሉ፣ ደጋፊና ገቢ የሌላቸው ነዋሪዎችን ለመደገፍ ሁልጊዜ በበዓላት ወቅት የማዕድ ማጋራት ተግባራችንን አጠናክረን እንቀጥላለን ብለዋል።

የሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ፣ የፌቤላ ዘይት ፋብሪካ፣ የአኮርዲያ ትሬዲንግና ኢንቨስትመንት ፒ ኤል ሲ፣ የአቪድ ግሩፕ እና አትሌት እጅጋየሁ ዲባባ ‘መስጠት አያጎድልም’ ብለው ካላቸው ቀንሰው ለወገኖቻችን ማዕድ እንድናጋራ ስላገዙን አመሰግናለሁ ብለው፤ ለመላው የክርስትና እና የእስልምና እምነት ተከታዮች መልካም በዓል ተመኝተዋል።

# ልዩ ኃይሎችን እንደገና ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ግን እየተነሱ ያሉ ስጋቶችም ሆኑ የአንድ ክልልንም ልዩ ኃይል ለማፍረስ ያለመ ነው የሚለው ሀሳብ መሠረተ ቢስ መሆኑን ገልጸዋል።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከቀናት በፊት ባጋሩት ጽሑፍ እንደገለጹት፤ የአንድ አገር ሠራዊት ጥንካሬ የሚወሰነው በዋናነት በማዕከላዊነቱና በጠንካራ የዕዝ ሰንሰለቱ ነው።

አሥር ቦታ ተበጣጥሶ ከተዋቀረ መቶ ሠራዊት ይልቅ በአንድ ማዕከል በሥርዓት የተደራጀ ሠላሳ ሠራዊት ይበልጥ ጠንካራ እንደሚሆን ያስገነዘቡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በመከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት የቁጥር ብልጫ የሚጫወተው የራሱ ሚና እንዳለ ቢታመንም፤ ቁጥሩ በጠንካራ የዕዝ ሰንሰለት፣ በጥብቅ ዲሲፕሊን፣ በተደራጀ ስትራቴጂና በረቀቁ መሣሪያዎችና ሥልጠናዎች እስካልታገዘ ድረስ የሠራዊት አቅም አስተማማኝ ሊሆን አይችልም ብለዋል።

ሀገራት በማዕከላዊ የፀጥታና ደህንነት ተቋማት አማካኝነት የሚጋረጡባቸውን ሥጋቶች መመከት የማይችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር እንደ ሚሊሻና ልዩ ኃይል ያሉ አነስተኛና መካከለኛ የጸጥታ ኃይሎችን አደራጅተው ለመንቀሳቀስ የሚገደዱበት ዓለም አቀፋዊ ልምድ መኖሩን የሚያስታውሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ሁኔታዎች ሲቀየሩ ዘላቂ ጥቅም የሚያስገኙ የመፍትሔ አማራጮች ቦታ ቦታቸውን እንዲይዙ ማድረግም አስፈላጊ እርምጃ መሆኑ አያጠያይቅም ሲሉ አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በሪፎርምና በውጊያዎች ጠንክሮ እየተገነባ ይገኛል የሚሉት ዶክተር ዐቢይ፤ የመከላከያ ሠራዊትን ማዕከላዊ በሆነ መልኩ ማጠናከርና ለሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲበቃ ማድረግ ተገቢ ነው። ይህንን መሠረት በማድረግ የክልል ልዩ ኃይሎች የሀገር መከላከያ ሠራዊቱን እንዲቀላቀሉ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

ወደ መከላከያ ሠራዊት ለመቀላቀል ያልፈለጉ ደግሞ ወደ ፌደራል ፖሊስ ወይም ወደ ክልሎች ፖሊስ እንዲገቡ ምርጫ ተቀምጦላቸዋል፤ ከዚህም አልፎ ወደማኅበረሰቡ ገብተው በሲቪል ለመቀጠል ለሚፈልጉም አማራጮች ቀርቦላቸዋል ።

የየክልሉ ልዩ ኃይሎች ኢትዮጵያ አስቸጋሪ ፈተና በገጠማት ጊዜ ሕይወታቸውን መሰዋታቸውን የሚጠቅሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የልዩ ኃይል አደረጃጀት አስፈላጊ አይደለም ማለት የልዩ ኃይል አባላት አያስፈልጉም ማለት አይደለም። ለወደፊቱም በተሻለና ይበልጥ ኢትዮጵያን ማገልገል በሚያስችላቸው ቦታዎች ላይ እንደ የፍላጎታቸው ተመድበው ማገልገል የሚችሉበት እድል መፈጠሩንም ያስገነዝባሉ።

ኢትዮጵያ ከክልል ልዩ ኃይሎች ጋር በተያያዘ ከአንዴም ሁለት ጊዜ የሀገርን ሉዓላዊነትና አንድነት የተገዳደሩ ፈተናዎች ገጥመዋት እንደነበር አስታውሰው፤ ከአንድነትና ሉዓላዊነት ሥጋትነት በመለስም በክልሎች መካከል የማያስፈልግ ተፎካካሪነትና ተገዳዳሪነት እንዲፈጠር መንስኤ ሲሆኑ መታየቱንም አንስተዋል።

ከዚህም ባለፈ ከሕገ ወጥ የኬላ ዝርጋታ፣ ከኮንትሮባንድ፣ ከሽፍትነት፣ ወዘተ ጋር የተያያዙ ፈተናዎችም እየተስተዋሉ በመሆኑ ለዘላቂ ሀገራዊ ጥቅም ሲባል ነገሮችን በአግባቡ ፈትሾ አስፈላጊውን የመፍትሔ እርምጃ መውሰድ ተገቢ መሆኑን አውስተዋል።

ካጋጠሙን ፈተናዎች በመነሣት ልዩ ኃይሎች ወደ መከላከያ እንዲጠቃለሉ ሕዝቡ ጠይቋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ የልዩ ኃይል አባላትም ከሜካናይዝድ ሥልጠና፣ ከደመወዝ፣ ከማዕረግ ዕድገት፣ ከትምህርት ዕድሎችና ከሌሎችም ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ነገሩን በተደጋጋሚ አንስተውታል። አብዛኞቹ ክልሎችም ሠራዊት ለማስተዳደር የሚያስችል የኢኮኖሚ አቅም የላቸውም ብለዋል።

ውሳኔው ሁሉንም ክልሎች ባካተተ መልኩ ስምምነት ላይ የተደረሰበት መሆኑን አመላክተው፤ የአንድ ክልልን ለመጉዳት ሌላውን ለመጥቀም ታስቦ የተደረገ አስመስሎ የሚነዛው ሀሳብ ግን ከእውነት የራቀ መሆኑን አስረድተዋል።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ከሰሞኑ በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በሀገር ደረጃ በሁሉም ክልሎች የሚገኙ ልዩ ኃይሎችን በፌዴራል የፀጥታ ተቋማት ለማደራጀት ተወስኖ ወደ ትግበራ ተገብቷል።

ውሳኔው በፌዴራል መንግሥት እና በክልል መንግሥታት ስምምነት የተወሰነ መሆኑንም የሚናገሩት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ውሳኔው በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ የሚደረግ እንደሆነም ገልጸዋል።

በአማራ ክልልም ውሳኔውን ለመተግበር እየተሠራ መሆኑን ያስታወሱት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በአፈጻጸም ላይ በታየ ክፍተት እና በተነዛው ፕሮፖጋንዳ ችግሮች ተከስተዋል ሲሉም አብራርተዋል።

ችግር እንኳን ቢኖር ተወያይቶ መፍታት እንደሚቻል ያስገነዘቡት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የአማራ ልዩ ኃይል ከመከላከያ ሠራዊት ጋር ሆኖ የሀገርን ሕልውና እና ሉዓላዊነት የጠበቀና ያስከበረ ነው፣ ውሳኔው ልዩ ኃይልን ትጥቅ የሚያስፈታና የሚበትን ሳይሆን በላቀ አደረጃጃት ኃላፊነቱን እንዲወጣ የሚያስችል ነው ብለዋል።

የአማራ ሕዝብ በሁኔታው ቅሬታ ውስጥ መግባቱን የተናገሩት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ቅሬታው የመነጨው በተሟላ መንገድ ለሕዝቡ መረጃ ባለመድረሱ እንደሆነም አብራርተዋል።

ዓላማው የሀገር አንድነትን የሚያጸና፣ አብሮነትን የሚያስቀጥል እና የጸጥታ መዋቅሩ በክልልም ሆነ በፌዴራል የተናበበና ሕግን መሠረት ያደረገ እንዲሆን ማድረግ ነው ብለዋል።

የአማራ ክልልን ልዩ ኃይል በተለየ መንገድ ትጥቅ ለማስፈታት እና ለመበተን የታለመ ዓላማ እንደሌለ አስገንዝበው፤ የአማራ ክልል ሕዝብ ጉዳዩን በውል በማጤን፣ በመመካከርና ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት አስቀድሞ በማሰብ መስከን እንደሚገባም አሳስበዋል።

የአማራ ልዩ ኃይል በተለየ መንገድ የሚጎዳ ውሳኔ አልተወሰነም ያሉት ዶክተር ይልቃል፤ ውሳኔው በሁሉም ክልሎች የሚፈጸምና ለሀገር ግንባታ ታላቅ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው በመገንዘብ የክልሉ ልዩ ኃይሎች ለሀገራችሁ እና ለክልላችሁ ስታደርጉት የነበረውን አስተዋፅዖ በተሟላ መንገድ ለማስቀጠል እንድትችሉና እንድትዘጋጁ አደራ እላለሁም ብለዋል።

የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ አባልና የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ግርማ የሺጥላ እንደሚሉት ደግሞ፤ የአማራ ልዩ ኃይል መከላከያ ሠራዊት በተከዳበትና ሀገር ሕልውናዋ አደጋ ውስጥ በገባበት ወቅት መስዋዕትነት የከፈለ መሆኑን አስታውቀዋል።

አቶ ግርማ ከአሚኮ ጋር ባደረጉት ቆይታ እንዳሉት የልዩ ኃይል ሪፎርም የሚካሄደውም የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት የሚያረጋግጥ፣ የሀገርን አንድነት የሚያጸና ጠንካራ የጸጥታ ኃይል ለመገንባት ነው።

የልዩ ኃይል ሪፎርምን ተከትሎ በአማራ ክልል የተፈጠሩ አለመግባባቶች ምክንያታቸው ጉዳዩን በሚመለከት የግንዛቤ ሥራ በአግባቡ ባለመሠራቱ ነው ያሉት አቶ ግርማ፤ የክልል ልዩ ኃይሎችን ሪፎርም የማድረጉ ጉዳይ የቆየ ውሳኔ ቢሆንም በሰሜኑ ግጭት ምክንያት ትግበራው መዘግየቱን አብራርተዋል።

በክልሉ መከላከያ ሠራዊት ሲንቀሳቀስ ሌላ ኃይል እንደገባ ተደርጎ የሚሠራጨው አጀንዳ አንድ ጠንካራና ወጥ መከላከያ ለመገንባት የሚደረገውን ሂደት የሚጎዳ እንደሆነም ገልጸው፤ ወደ አማራ ክልል ምንም አይነት የተለየ ኃይል እንዳልገባም አረጋግጠዋል።

የአማራ ሕዝብ የደረሰበትን መፈናቀል፣ ሞት እና አለመረጋጋት የክልሉ መንግሥትና ብልጽግና ፓርቲ በልዩ ትኩረት ችግሩን ለመፍታት እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይም ከክልሉ መሪዎች እውቅና ውጭ ከልዩ ኃይል ሪፎርም ጋር በተያያዘ በማኅበራዊ ሚዲያ ልዩ ኃይሉ ትጥቅ እንደሚፈታ ተደርጎ የተሠራጨው መረጃ ትክክል አይደለም። በሪፎረሙ ትጥቅ ስለመፍታት የተላለፈ ውሳኔ የለም ብለዋል።

“የአማራ ልዩ ኃይል በክልሉ ሕዝብና መንግሥት ትልቅ ዋጋ ተከፍሎበታል፤ ይህ ኃይልም ፖለቲካዊ ትርጉሙ ከፍ ያለ ነው” ያሉት አቶ ግርማ፤ “ይልቁንስ የሀገርና የሕዝብ አለኝታነቱን ይበልጥ የሚያሳይበትን አደረጃጀት ተከትሎ እንዲደራጅ ይደረጋል” ብለዋል ።

የአማራ ክልል በጦርነት ውስጥ የቆየ ነው፤ የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች እየተከናወኑ በመሆኑ እነዚህ ተስፋ ሰጭ ሥራዎችም መሰናከል የለባቸውም ብለዋል።

መንግሥት የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ ለማደራጀት የጀመረው እንቅስቃሴ አዲስ የተጀመረ ሳይሆን ከሦስት ዓመት በፊት ውሳኔ የተላለፈበትና በወቅታዊ የሃገሪቱ ችግሮች ምክንያት ተግባራዊ ሳይደረግ የቆየና በአሁኑ ወቅት በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች በሰፈነው አንጻራዊ መረጋጋት ወደተግባር እየተገባበት ያለ ጉዳይ መሆኑም ተገልጿል።

መልሶ ማደራጀቱ በአንድ በኩል በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች ዘላቂ ሰላምን ለማጽናትና አልፎ አልፎ በክልሎች መካከል የሚታዩ አላስፈላጊ የኃይል ፉክክሮችን ለመግታትና ፉክክሩን በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ እንዲሆን ለማድረግ የታለመ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ጠንካራ ኅብረብሔራዊ ሠራዊት ለመገንባት ትልቅ እርምጃ ነው። ከዚህም ባሻገር ክልሎችን ለልዩ ኃይሎች ከሚያወጡት አላስፈላጊ ወጪ በመታደግ በጀታቸውን ለልማትና ለሕዝብ ልማት እንዲያውሉ ዕድል የሚሰጥ ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በማዕድ ማጋራት እየጎለበተ የመጣው የኢትዮጵያውያን የመደጋገፍና መረዳዳት እሴት!

ኢትዮጵያውያን በመረዳዳትና በመደጋገፍ ይታወቃሉ፤ ባሕላቸውም ነው። መረዳዳትና መደጋገፉ ሰው ባጣ በነጣ ጊዜ ካላቸው በማካፈል፣ ይህ ቀን ያልፋል፤ አይዞህ በማለት የሞራል ስንቅ በመስጠት ሲያረጋግጡት ኖረዋል።

መደጋገፍና መረዳዳቱ ያጣንና የተቸገረን በመደገፍ ላይ ብቻ የተመሠረተ አይደለም፤ ከዚህም ይሻገራል። ተረዳድቶ ሰውን ሰው ማድረግ ሌላው እሳቤ ነው። ሰዎች ተረባርበው ሰውን ሰው ያደርጋሉ፤ ልጆች ያስተምራሉ፤ ሥራ ያስጀምራሉ፤ የደከመ ካለ ቀና እንዲል ያደርጋሉ፤ ሥራ ያጣን ሥራ ያስጀምራሉ። ይህ የኢትዮጵያውያን ተፈጥሯዊ ባሕሪ ነው።

ይህ የመደጋገፍ፣ የመስጠትና የመረዳዳት ባህል በክፉ ቀን ሲሆን ደግሞ ከዚህም ይልቃል፤ ይህ በጎ ተግባር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በተለይ በበዓል ወቅቶች እየጎለበተ መጥቷል። በጠቅላይ ሚኒስትሩና በተለያዩ የመንግሥት ኃላፊዎች ሳይቆራረጥ እየተፈጸመ ያለው በችግር ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ማዕድ የማጋራት ተግባር እዚህ ላይ ሊጠቀስ ይገባዋል። ከሃገራዊ ለውጡ አንስቶ ባለፉት አምስት ዓመታት ይህ የኢትዮጵያውያን የመስጠት፣ የመረዳዳትና መደጋገፍ ባሕል ይበልጥ ለማጠናከር የበኩሉን ሚና እየተጫወተ ነው።

በሃገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በደረሱ ግጭቶች ሳቢያ ከቤትና ቀያቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች ኢትዮጵያውያን የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረጋቸው ሁሌም ይታወሳል። በዚህ ተግባር በሃገር ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ብቻም ሳይሆኑ በውጭ የሚኖሩትም በመሳተፍ ከወገኖቻቸው፣ ከመንግሥታቸውና ከሃገራቸው ጎን ቆመዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት ባለሀብቶችን፣ ድርጅቶችን፣ ወዘተ በማስተባበር በተለይ ዓመት በዓል በመጣ ቁጥር በችግር ውስጥ ለሚኖሩ ዜጎች ማዕድ በማጋራት የፈጸሙት ሰብዓዊ ተግባር ትርጉሙ ብዙ ነው። ይህ አርአያነት ያለው ድጋፍ ክልል ከተሞች ድረስ እየዘለቀም ይገኛል። የክልል መሪዎች፣ ከንቲባዎችና የተለያዩ ተቋማት ኃላፊዎች ሕዝቡን፣ ባለሀብቶችን፣ ድርጅቶችን እያስተባበሩ ችግረኞች ዓመት በዓልን ደስ ብሏቸው እንዲያሳልፉ እያደረጉ ናቸው።

በዚህ በጎ ተግባር እነዚህ ዜጎች ዓመት በዓልን ደስ ብሏቸው እንዲያሳልፉ ማድረግ ተችሏል፤ በበዓል ወቅት ምግብ ከመቋደስም ባለፈ ኑሮን ለመደጎም ያስቻለም ነው፤ በአምስት ዓመታት ውስጥ በሁሉም ዋና ዋና የሃይማኖት በዓላት ወቅት ይህ ድጋፍ ተደርጓል፤ ድጋፉም እየሰፋ መጥቷል። ሌሎች ኢትዮጵያውያንም በክፉ ቀን የሚደርሱላቸው ወንድሞች እህቶች እናቶችና አባቶች ልጆች እንዳሏቸው እንዲረዱ አድርጓል።

ድጋፉ ከተደረገላቸው ዜጎች በስተጀርባ ያሉ ሕጻናት ፣ እናቶች፣ አባቶች፣ ወዘተ. ሲታሰቡ ደግሞ ድጋፉ ምን ያህል ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም። ከሁሉም ከሁሉም በላይ ደግሞ የኢትዮጵያውያንን የመረዳዳትና መደጋገፍ ባሕል በሚገባ ማስጠበቅ ያስቻለ ብቻ ሳይሆን የመስጠትን፣ የመደገፍንና የመርዳትን አስፈላጊነትና ታላቅ ተግባርም ያስተማረም ነው።

በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ኪስ ውስጥ ለእነዚህ በከፋ ችግር ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች ሊሆን የሚችል ሀብት ስለመኖሩ ጥርጥር የለውም፤ ይሁንና የመስጠትን፣ የመርዳትና የመደገፍን ጽንሰ ሀሳብ ባለመረዳት፣ ምናልባትም ለጉዳዩ በቂ ትኩረት ካለመስጠት የተነሳ ጥቂት የማይባሉ ዜጎች ይህን ታላቅ እሴት ያላጤኑበት ሁኔታ ይስተዋላል። ሁሉም ዜጎች በዚህ ጉዳይ ላይ ግንዛቤው እንዲኖራቸው ማድረግ ላይ በመሥራት ለእነዚህ በከፋ ችግር ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች ተጨማሪ ድጋፍ ማስገኘት ይቻላል።

ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንደሚገነዘበው ኢትዮጵያውያን ይረዳዳሉ፤ ይደጋገፋሉ፤ ይሰጣሉ። መረዳዳቱ፣ መደጋገፉና መተጋገዙ ግን ከቤተሰብ፣ ከጎረቤት ከአቅራቢያ ብዙም የተሻገረ ነው ብሎ ማለት አይቻልም፤ ይህን በጎ ተግባር ማሻገር ላይ መሥራት ያስፈልጋል። ችግሩ ደጅ እስከሚመጣ፣ መንገድ ላይ እስከሚታይ መጠበቅም አይገባም፤ እንደ ታዳጊ ሃገር ባለው የምጣኔ ሀብት ውስንነት በከፋ ችግር ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች በርካታ ናቸው። እነዚህ ዜጎች የመንግሥትን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያውያንን የቅርብ ድጋፍ ይፈልጋሉ። ይህን ማስገንዘብ ላይ መሥራት ለነገ ሊባል የሚገባው ተግባር አይደለም።

የእያንዳንዱ ዜጋ ድጋፍ እንዳለ ሆኖ ድጋፉ የተደራጀ እንዲሆን ማድረግ ላይ መሥራትም ይገባል፤ ሜቄዶኒያና ሌሎች ተመሳሳይ የበጎ አድራጎት ተቋማት ለእዚህ ትልቅ ትምህርት ቤት ናቸው። እነዚህን የመሳሰሉ ተቋማት በማቋቋም ዜጎችን አሰባስቦ በኅብረት መርዳትም ይቻላል።

አንዳንድ ባለሀብቶች እንደሚያደርጉት ሌሎች ባለሀብቶችም በዓመት ከሚያገኙት ትርፍ የተወሰነውን ለዚህ ታላቅ ተግባር እንዲያውሉ ቀርቦ ማስረዳት፣ ድጋፍ ያደረጉ ባለሀብቶችን በጎ ተግባር እንዲመለከቱት ማድረግ ላይ መሥራት ያስፈልጋል።

ሁሉም ዜጎች የሌሎች ዜጎች ሕመም እንዲሰማቸው ማድረግ ላይ ከትምህርት ቤት ጀምሮ መለማመድም ሌላው ሊሠራበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ለእዚህ ደግሞ በማዕድ ማጋራት፣ በኢትዮጵያውያን በተቋቋሙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እየተከናወኑ የሚገኙ ተግባሮችን የተመለከቱ መረጃዎች እንዲደርሷቸው ማድረግ በትምህርት ቤታቸው ለእዚህ ተግባር የሚሠሩ ክበባትን በማቋቋም ላይ ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባል። ይህ ሁሉ ሲሆን የኢትዮጵያውያን የመደጋገፍ፣ የመረዳዳትና የመስጠት እሴት ይበልጥ እየጎለበተ ይሄዳል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የበዓል ገበያውን ለማረጋጋት

ዳንኤል ዘነበ

በሀገሪቱ የኑሮ ወድነቱ ከወር እስከ ወር ከዓመት እስከ ዓመት በየጊዜው ማሻቀቡና ተባብሶ መቀጠሉን የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት በየጊዜው የሚያወጣቸው መረጃዎችና በማኅበረሰቡ ላይ የሚታየው የኑሮ ጫና ያመላክታል። በየጊዜው እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ወድነት አሁን ላይ በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የማኅበረሰብ ክፍል ኑሮ በእጅጉ እየፈተነ ይገኛል።

በኢትዮጵያ ከመሠረታዊ የምግብ ፍጆታዎች እስከ ሌሎች ቁሳቁሶች ድረስ የዋጋ ግሽበቱ በየጊዜው እያሻቀበ ቢሆንም፣ የአብዛኛው የማኅበረሰቡ ክፍል ገቢ ወይም የመግዛት አቅም ግን ከዋጋ ግሽበቱ እኩል ማደግ አልቻለም። የአፍሪካ ዴቨለፕመንት ባንክ መረጃ እንደሚያመለክተው ፤ የኢትዮጵያ ምጣኔ ሃብት በፈረንጆቹ 2021 ከነበረው 6 ነጥብ 1 ዕድገት ዝቅ ብሎ በ2022 ወደ 5 ነጥብ 6 ወርዷል ። የኑሮ ግሽበቱ ደግሞ በ2021 ወደ 26 ነጥብ 7 በመቶ ከፍ ብሏል ።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች እንደሚሉት፣ የኑሮ ወድነት ተከሥተ የሚባለው የማኅበረሰቡ የመግዛት አቅም ወይም ገቢ ማነስ ከዋጋ ግሽበት ጋር ተደምሮ የሚፈጥረው የመግዛት አቅም መዳከም ነው። ከዚህ አንጻር በአገሪቱ የምግብ ነክ ሸቀጦች የዋጋ ግሽበት፣ የምንዛሬ እጥረት፣ የትምህርት ቤት ክፍያዎች ማሻቀብና ሌሎችም ማኅበረሰቡን እየተፈታተኑ ከሚገኙት ችግሮች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

መንግሥት ከወዲሁ ችግሩን ለመፍታት የተለያዩ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን እያደረገ ቢሆንም የሸቀጦች ዋጋ ህዝቡ በሚጠብቀው መልኩ ሊወርድ አልቻለም። የአገራችን ገበያ የመጨመር እንጂ የመቀነስ ባህሪ እያሳየ አይደለም። የሸቀጦች ዋጋ መሸቶ በነጋ ቁጥር ጨምሮ ያድራል እንጂ ቀንሶ ሲያድር አይታይም ።

በየጊዜው በሸቀጦች ላይ የሚታየው የዋጋ ጭማሪ ደግሞ መዘዙ እንደ ቱባ ክር የሚመዘዝ በመሆኑ ብዙ ችግሮችን ይወልዳል። የግለሰቦችን የመግዛት አቅምን ከማዳከም አልፎ የተቋማትን አቅም እየፈተነ ይገኛል። ይህ እየሆነ ባለበት፤ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በታላቅ ድምቀት የሚከበረው የፋሲካ በዓል ጥቂት ቀናት ቀርተውታል።

በዓሉን ደግሞ ከቤተሰብ እስከ ወዳጅ ዘመድ ተሰባስቦ ማክበር የተለመደ እንደሆነ ይታወቃል። ይህ እንደመሆኑ ዘመድ አዝማድ በዓሉን በጋራ የሚያከብረው ለቀኑ የሚሆኑ አልባሳትን ፣ ምግብ እና መጠጦች ከወትሮው በተለየ ሁኔታ አዘጋጅቶ እንደሆነ ይታወቃል። ስለዚህ ሁሉም እንደ አቅሙ በተለያየ መልኩ ቀደም ብሎ ይዘጋጃል። የበዓል ሸመታ ያደርጋል። በዚህም የተነሳ የበዓል ገበያው ይጦፋል። ይህ በራሱ ለበዓሉ አንድ ደማቅ ድባብ የሚፈጥር መሆኑ አይካድም።

ይሁን እንጂ በዓላት በደረሱ ቁጥር የሚደረጉ ተገቢ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪዎች ፤ በአገራችን አሁን ካለው ከፍተኛ የኑሮ ውድነት ጋር ተደምሮ የሸማቾች ዋነኛ ሥጋት ከሆኑም ሰነባብተዋል። የበዓል ገበያን ከሚረብሹ ሀይሎች መካከል ደግሞ በዋነኛነት የሚጠቀሰው የደላላ ጣልቃ ገብነት ነው።

በተለያዩ የማኅበራዊ ትስስር ገጾች በደላሎችና በተባባሪዎቻቸው የሚሠራጨው የዶሮ፣ የበግ፣ የፍየልና የዕርድ የበሬ ዋጋ የበዓሉን ድባብ ከመረበሹም በላይ፣ ሸማቾችና ነጋዴዎች ተሳስበው ግብይት እንዳይፈጽሙ ያግዳቸዋል። ይህን ተከትሎ የበዓል ገበያው ከወትሮው የተለየ መሆኑ ደግሞ ሌላ ተደራቢ ችግር ሆኗል ።

የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በታላቅ ድምቀት የሚከበረውን የፋሲካ በዓል ገበያውን አነሳን እንጂ ዋነኛው ጉዳያችን እሱ አይደለም። የበዓል ገበያውን ምክንያት ያደረጉት የዋጋ ጭማሪዎች ከበዓል በኋላስ ? የሚለው ነው። ምክንያቱም በአገራችን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ጉዳዩን ቀለል አድርጎ ማየት የሚገባ አይሆንም።

ከበዓል በፊት 13 ብር የነበረው የአንድ እንቁላል ዋጋ በበዓል ገበያው ወደ 16 ብር ያድጋል ። በበዓል ግርግር የጨመረው የእንቁላል ዋጋ በአንድ ጊዜ ሦስት ብር እንደጨመረ አልያም ከዚያም በላይ በሆነ ጭማሪ በአዘቦትም ይቀጥላል ። ታዲያ መውጣት እንጂ መውረድ በማያውቀው የአገራችን የገበያ ሁኔታ ፤ የበዓላት መምጣት ከደስታ በላይ ሰቀቀንን እየፈጠሩ ይገኛል ።

መንግሥት የአቅርቦት ሰንሰለቱ በደላሎች ጣልቃ ገብነት ሳይታወክ ግብይት እንዲከናወን የቁጥጥር ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያደርገው ጥረት ከችግሩ መገንገን፤ ሌሎችም ወቅታዊ ፖለቲካ ጉዳዮች አንጻር ብዙም ውጤታማ ነው ለማለት አይቻልም። በርግጥ ጤናማ የግብይት ሥርዓት ሊኖር የሚችለው የመንግሥት፣ የአምራቹ ፣ የሸማቾችና የነጋዴው መስተጋብር አግባብ ሲኖር ነው። ሁሉም የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ሲችል ፤ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነት ሲላበስ ነው።

የንግዱ ማኅበረሰብ ከፍ ካለ ራስ ወዳድነት ሊወጣ፤ ስለ ሸማቹ ህብረተሰብ ኃላፊነት ሊሰማው ይገባል። ኃላፊነት የተሞላበት ሀገራዊ የግብይት ስርአት እንዲኖረው የራሱን ኃላፊነት መወጣት ይኖርበታል። የበዓል ሰሞን ገበያ በርካታ ሸማቾች የሚንቀሳቀሱበትና ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ የሚዘዋወርበት በመሆኑ፣ ነጋዴዎች ከብዛት የተሻለ ትርፍ ስለሚያገኙ አላስፈላጊ ከሆነ የዋጋ ጭማሪ መታቀብ ይጠበቅባቸዋል። ማህበረሰቡም የጊዜውን ሁኔታ እና አቅሙን በሚመጥን መንገድ በአቅሙ ሸምቶ በዓሉን በደስታና በአንድነት ማክበር ይኖርበታል ።

መንግስትም ቢሆን በበዓል ገበያው የምርት እጥረት እንዳይከሰት እና ተገቢ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪዎች እንዳይኖሩ የተለዩ አማራጮችን ማቅረብ ይጠበቅበታል። ለአብነትም የበዓል ገበያውን ለማረጋጋት የተለያዩ የግብርናና ኢንዱስትሪ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በገበያዎች እና በዓሉን ታሳቢ በማድረግ በተከፈቱ ባዛሮች እንዲቀርቡ ማበረታታት ይኖርበታል። አሁን እንደተጀመረው ተፈላጊ ምርቶችን ከዩኒየኖች እና አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ከአርሶ አደሩ ጋር በመነጋገርና በስፋት ለሸማቹ ህብረተሰብ የሚቀርቡበትን አሰራር አጠናክሮ መቀጠል የግድ ይላል።

ከዚህ በተጨማሪ የበዓል ገበያውን ለማረጋጋት ከሚወሰዱ እርምጃዎች በተጓዳኝ በአገሪቱ የተፈጠረውን የኑሮ ውድነት ለመቆጣጠር ገበያን በዘላቂነት ማረጋጋት የሚያስችሉ በጥናት ላይ የተመሰረቱ ዘላቂ መፍትሄዎችን ማፈላለግ ያስፈልጋል። ምርትን በመሰወር የገበያ እጥረት በመፍጠር ያለ አግባብ የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉ እና ሰው ሰራሽ የምርት አቅርቦት እጥረት የሚፈጥሩ አካላት ላይ የማያዳግሙ እርምጃዎችን በመውሰድ እነዚህ አይነት ያልተገቡ ልምምዶች መቋጫ እንዲያገኙ ማድረግም ያስፈልጋል።

# ነፃ ሃሳብ

# አንድ መከላከያ፤ አንዲት ጠንካራ አገር

**ታምራት ተስፋዬ**

በኢትዮጵያ የሚገኙ ክልሎች «ልዩ» በሚል ስያሜ የፖሊስ ኃይል ማደራጀት የተጀመረው በሚሊኒየሙ መግቢያ በሶማሌ ክልል ከኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦብነግ) ጋር ከነበረው የሽምቅ ውጊያ ጋር በተያያዘ መሆኑን የታሪክ ድርሳናት ይጠቁማሉ። ባለፉት አመታትም ፉክክር በሚመስል መልኩ ክልሎች ልዩ ኃይል እንደ መደበኛ ሠራዊት ሲያሰለጥኑ እና ሲያስታጥቁ ከርመዋል።

ይህ የኃይል አደረጃጀትም ሁለት ዓይነት አስተያየትን ሲያስተናግድ ቆይቷል። አንደኛው «ክልሎች የራሳቸውን ልዩ ኃይል አደራጅተውና አስታጥቀው ማሰማራታቸው ለአገር ደኅንነት አደጋ ነው፤ የእነዚህ ኃይሎች አደረጃጀትም ሕጋዊ መሠረት የሌለው ነው» የሚል ነው። ሌላኛው ደግሞ የልዩ ኃይል ፖሊሶችን ጥቅም ከግምት በማስገባት የአንድን ክልል ሕዝብ ደኅንነት ለማስጠበቅ ከፖሊስ ባሻገር ይህ ሠራዊት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበርክት እንደሚችል የሚሞግት ነው።

ከልዩ ኃይል አመሠራረት ጋር አብሮ ከሚነሱት ጉዳዮች መካከል አንዱ ሕጋዊ መሠረቱ ነው። የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 52 የክልሎች ስልጣንና ተግባር ይደነግጋል። የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 52/2/ሰ ክልሎች የክልላቸውን የፖሊስ ኃይል ያደራጃሉ፣ ይመራሉ፣ የክልሉን ሰላምና ጸጥታ ያስጠብቃሉ ይላል። ይሁን እንጂ ይህን የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ አንዳንዶች በፈለጉት መልኩ ይተረጉሙታል።

ይሁንና ክልሎች ሰላምና ጸጥታ የሚያስከብሩት መደበኛ ፖሊስን ተጠቅመው እንጂ ከመደበኛ ፖሊሱ በተጨማሪ ሌላ የልዩ ኃይል ፖሊስ እንዲያደራጁና እንዲያሰማሩ ፈቃድን አይሰጥም። ምንም እንኳን ከትጥቅ አያያዝና አደረጃጀት ጋር የተያያዘ ግልጽ ፖሊሲን ባያስመለክትም፣ ከተልዕኮ አንፃር የፖሊስ ሰራዊቱ መያዝ የሚገባው ትጥቅና አደረጃጀት ከአገር መከላከያ ሰራዊትም በላቀ መልኩ መሆን አለበት እንደማይል ለመረዳት የሕገ መንግሥት ወይንም የሕግ ተንታኝ መሆን አይጠይቅም።

ይሁንና ቀደም ሲል አገር ይመራ የነበረው መንግሥት ይህን የሕግ አንቀፅ ለትርጉም እንዲጋለጥና ከፍ ሲልም በርካቶች ሲገልፁት እንደሚሰማው «ለራሱ እንዲመቸው» ክፍት አድርጎት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አትንኩብኝ ብሎ በመቆየቱ ክልሎችም በራሳቸው መንገድ ሲረዱት፣ ከሕግ አውድ ውጪም ሲተረጉሙት ቆይተዋል።

ይህ ተከትሎም ልዩ ኃይሎች የተቋቋሙበት ሕጋዊ መሠረት፣ ተጠያቂነታቸው፣ በሙያ ቀኖናቸው ፖሊስ ወይንስ ተዋጊ መሆን አለመሆናቸው፣ የልዩ ኃይሎችን ዕዝ ሰንሰለት፣ ብዛት፣ መሣሪያ ዓይነት፣ በሕግ የተደነገገ ሚና እንዲሁም ከፌዴራል ፖሊስም ሆነ ከመከላከያ ሰራዊት ጋር ስለሚኖራቸው የሥራ ግንኙነት ግልፅ ባለመሆኑ አጠቃላይ አደረጃጀቱ በየጊዜው የበርካቶች ትችት ተለይቶት አያውቅም።

አደረጃጀቱ የሚራመድበትም ሆነ የሚገራበት የሕግ እና ፖሊሲ መንገድ ባለመኖሩም ክልሎች በተለያዩ ጊዜያት በሚያካሂዷቸው ወታደራዊ ትዕይንቶች ላይ የልዩ ኃይል አባላቱ መካከለኛ እና ከባድ የነፍስ ወከፍና የቡድን የጦር መሣሪያዎችን ታጥቀው ታይተዋል።

የኃይል አደረጃጀቱ ብሔር ተኮር በመሆኑም አንደኛው ክልል ለሌላኛው አንደኛው ብሔር ለሌላኛው የሚቆም አልነበረም። ይህም አገር አቀፍ የሆነውን አብሮነት፤ የሕዝቦችን አንድነት በእጅጉ ሲሸረሽረው ታይቷል። በየክልሉ ያለው ልዩ ኃይል በስልጠና አወሳሰዱ፣ በትጥቁ፣ በሚወስዳቸው እርምጃዎችና በሚሰማራባቸው ተልዕኮዎች የወታደራዊ ኃይል ባህሪ ያለውና የዜጎችና ሰላምን ደህንነት ከማስጠበቅና ማስከበር ይልቅ ወደ ድንበር ጠባቂነቱ ሲያመዝንም ታዝበናል። አልፎ አልፎም ከፌዴራሉ መንግሥት የፀጥታ አካላት ጋር የጥይት እሩምታ እስከመለዋወጥ ከፍ ሲል ጦርነት እስከመግጠም መተላለፉ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው።

ገና ከጅምሩም ሆነ ከቅርብ አመታት ወዲህ የሚሆነው የሚያሰጋቸው በርካቶች የፌዴራሉ መንግሥት በየክልሉ ያሉትን የተደራጀና የታጠቀን ልዩ ኃይል በአግባቡ ማደራጀት እንዳለበት ሲሞግቱ፣ አደረጃጀቱ ተለውጦ ወደ መደበኛ ፖሊስ ወደ መከላከያ ሠራዊት ወይም ደግሞ ወደ ፌዴራል ፖሊስ ውስጥ እንዲጠቃለልና በዚያ ዕዝ ስር እንዲተዳደር በተደጋጋሚ ሲጠይቁ ቆይዋል።

ላለፉት አመታት ሰሚ ጆሮ የተነፈገው ይህ ጥያቄ በመጨረሻም በለውጡ መንግሥት ምላሽ ተሰጥቶታል። የአገሪቷን የግዛት አንድነት፤ የአገሪቷን ሉዓላዊነት፣ የአገሪቷን የሕዝቦች ደህንነት መነሻ በማድረግ መከላከያን ጨምሮ የተለያዩ የጸጥታ ኃይሎች ሪፎርም የመስራት ተግባር ቅድሚያ የተሰጠው ሲሆን ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታትም ይህ ተግባር በከፍተኛ ትኩረት ሲከናወን ቆይቷል። በአንድ በኩል ውስጥ ላይ የተቃጣውን ጥቃት የመመከት በሌላ በኩል ደግሞ ይሄንን ሪፎርም የመስራት ሥራ ተሠርቷል።

ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ጀኔራል አበባው ታደሰ ከሰሞኑ ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢቢሲ) ጋር በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ባደረጉት ቆይታ እንደገለፁትም፣ ሪፎርሙ የሚያጠነጥነው በኢትዮጵያዊነት የተገነባ ለሁሉም ሕዝብ እኩል የሆነ እና በቂ ችሎታ ያለው ዘመናዊ የጸጥታ ግብረ ኃይል እና መዋቅር መገንባት ነው። ይህ ኃይል ምንድን ነው የሚዘምነው? ለምንድን ነው ይህ ኃይል ሪፎርም እየተደረገ ያለው ? ለሚለው ግን አገሪቷ ሁለት ስጋቶች ስላሉባት ነው።

አንደኛው ስጋት ከባቢያችን ነው። «ሆርን አፍሪካ» የምንለው ስጋት ነው። ሁለተኛው በየጊዜው እየተቀያየረ የመጣው የዓለም ሁኔታ አገራችን ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ነው። እነኝህን ሊመክት የሚችል የጸጥታ መዋቅር ለመገንባት ነው። ሕዝብ በሰላም ወጥቶ በሰላም የሚገባባት፣ ልማት ያለምንም የጸጥታ እንቅፋት የሚሳለጥባት አገርን መፍጠር ነው።

በእርግጥ አገር ችግር ውስጥ ባለችበት ጊዜ ልዩ ኃይሎች የክልላቸውን ፀጥታ ይጠብቁ ነበር፤ ከመከላከያ ጋር ሆነው አብረው ሞተዋል። ቆስለዋል፤ ደምተዋል። ይሁንና የልዩ ኃይሉን ጥንካሬ መስዋዕትነትና ልፋት እንዳለ ሁሉ በሌላ በኩል እጥረቶችም አሉ። እጥረቶችን የሚገልፁ ማሳያዎች ምንድን ናቸው? ካልን ሕገ-መንግሥት ነው፤ ከሕገመንግሥት አንፃር ስናይ እነዚህ ኃይሎች ሕጋዊ አይደሉም። ሕገመንግሥቱ እውቅና አይሰጣቸውም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ማወቅ ያለበት በአገሪቷ የፀጥታ ኃይል እንዲገነባ የሚፈቅደው ሕግ መንግሥት መከላከያና ፌዴራል ፖሊስን ነው። ከመከላከያ ውጪ የታጠቀ ኃይል ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር የለበትም። የታጠቀ ኃይል ሕግ የሚፈቅደው መከላከያ እና የብሔራዊ ደህንነቱ ነው። ከዚህ ውጪ ሕገመንግሥቱ ላይ መብት የተሰጠው የለም። በሌላ አነጋገር ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹሙ እንዳሉት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ 14 ሬንጀር መመስረት አይቻልም።

አሁን ላይም የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ለማስጠበቅ እና አንድነቱ የተጠናቀረ እንዲሆን በሚል መልሶ ኃይሉን የማደራጀት ሥራ በየክልሉ ተጀምሯል። በፕሮግራሙ መሠረትም በሕገ መንግሥቱ የፀጥታ ኃይል፤ መከላከያ፤ ፌዴራል ፖሊስ ይኖራል። በክልሎች መደበኛ ፖሊስ ይኖራል። ሲደመር ሦስት ሬንጀር ይኖራል።

እንደሚታወቀው ገደብ የሌለው ነፃነት ጥፋት ያመጣል። በኃበዝ አለቃ የሚመራ አገር ግድግዳው እንደዘመመ፣ ጣራው እንደተቀደደ፣ ማገሩ እንደላላ ደሳሳ ጎጆ ነው። የጊዜ ጉዳይ እንጂ ጎጆው መፍረሱ አይቀርም። ይህ እንደመሆኑ የመንግሥት ውሳኔ ፋይዳው ዘርፈ ብዙ ነው።

ከሁሉ በላይ ብሔርን የማያይ፤ ዘርን የማይመርጥ ኢትዮጵያዊ የሆነ የፀጥታ መዋቅር ይገነባል። በዚህ መልክ የተዋቀረ ኃይል መኖሩም ከማንም በላይ የአገር ሉአላዊነትና ደህንነት እንዲሁም የሕዝቡን የሰላም ዋስትና ያረጋግጣል። መከላከያውም በየመንደሩ በየክልሉ ከሚደራጀው ኃይል ጋር ፖለቲከኛው ባመፀ ቁጥር ከመጋጨት እረፍት ያገኛል።

ይህን ውሳኔ አብዛኞቹ ክልሎችና የፀጥታ አካላት ተቀብለው ለውጤታማ ትግበራው ተባባሪ መሆናቸውን ከቃል ባለፈ በተግባር እያረጋገጡ ናቸው። በአንዳንድ አካባቢዎችም ከተግባቦት ውስንነትና ከኮሚኒኬሽን ችግር አንፃር በተዛባ መልኩ የመረዳት አዝማሚያ ታይቷል።

በተለይ በብሔር ፖለቲካ ልቦናቸው የተሰወረ፣ የአጥንት ፖለቲካን የሚወረውሩና ሕዝብን በማደናበር በማሳመፅ ፍላጎታቸውን ለማሳካት የሚታትሩ ተፈልፍለዋል። እጅጉን በሚያስተዛዝብ መልኩ አንዳንድ ግለሰቦችና የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ትናንት በይፋ የልዩ ኃይል አደረጃጀት ተፈትሾ ማስተካከያ ይደረግ ሲሉ ከርመው አሁን እሺ ሲባሉ የእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ እንዳለው ሲሆኑ እያስተዋልን ነው።

በአንዳንድ ማህበራዊ ሚዲያዎች፤ በአንዳንድ የፖለቲካና ወታደራዊ አመራሮች ላይ የሚነሱ አሉባልታዎች ወይም ደግሞ ስም የማጥፋት ዘመቻዎች እያስተዋልን እንገኛለን። እነዚህ የነገድ ፖለቲካ አራማጅ በመንደርተኛ አስተሳሰባቸው የሕዝብን ስሜት ለመቀስቀስ የሚጠቀሙበት ስልትም ተለዋዋጭ ነው። አንደኛው «ትጥቅህን አስፈትተው ሊበትኑህ ነው» የሚል ነው።

ይሁንና ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹሙ እንዳረጋገጡት እየተባለ ያለው ይህ አይደለም። ይልቁንስ ይህ ትልቅ ኃይል የኢትዮጵያ ኃይል ነው። እንጠቀምበት። ወደ ትክክለኛ ቦታውና ልኬታው እናምጣው ነው። እንበትነው አልተባለም፤ ትጥቁን እናስፈታው አልተባለም። የተባለው ሁሉንም እንደፍላጎቱ በአዲስ አደረጃጀት እናዋቅረው ነው። ውሳኔው ወደ መከላከያ ማስገባት፤ ወደ ፌዴራል መንግሥት ማስገባት፤ ወደ መደበኛ ፖሊስ ማስገባት ነው። በማን? በራሱ ምርጫ፤ በምን? ክብሩን በማይነካ፤ በምን? ሞራሉን በማይነካ፤ በምን? ጥቅሙን በማይነካ መልኩ።

ልዩ ኃይል ትጥቅ ሊፈታ ነው የሚለው ሀሰት ነው። እንዲያውም ሌላ መሣሪያ እንሰጠዋለን። የተባለው ሌላ ብረት እንሰጥሃለን እንጂ ትጥቅ ፍታ አይደለም። ያለም የለም። ከእኛ ጋራ ነው የምትከው ወደ ሕጋዊ መስመር እናስገባው እንጂ እንበትነው አላልንም።

ሌላኛው የውዥንብር አጀንዳ ደግሞ ማን ፈትቶ ማን ሊቀር ዓይነት ነው። እንደ እኔ እምነትም የአገር የማዕዘን ድንጋዩ ሁሉም ዜጋ የሚኮራበትና የሚንከባከበው እንጂ አንዱን አስኮርፎ ሌላውን የሚያስደስት አይሆንም። መርጦ የመስማት ትልቅ በሽታ የሌለበት ካልሆነ ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹሙ እንዳሉት፣ አንደኛው ክልል ኃይል እንዲኖረው ሌላው ክልል ግን ኃይል እንዳይኖረው አይደረግም።

ይሄ ኢትየጵያ ውስጥ አይታሰብም። ክልሎች ሊይዙት የሚችሉት ኃይል አንድ ነው፤ ይሄም መደበኛ ፖሊስ ነው። ከዚህ ውጪ አይዙም። መደበኛ ፖሊስ አድማ በታኝ ይኖራል ከዚህ ውጪ አይፈቀድም። ሕጉም አይፈቅድም።

አፈፃፀሙም እኩል የሚከወን ነው። አንደኛውን አሳብጦ አንደኛውን ማርገብ አይደለም። የታጠቁ ኃይሎች ትጥቅ ይፈታሉ። የትግራይ ክልል እንደማንኛውም ክልል የሚኖረው መደበኛ ፖሊስ ብቻ ነው። የታጠቀ ልዩ ኃይል የሚባል በፍፁም አይኖረውም።

አገርን ወደኋላ የሚጎትት የማይጠቅም አስተሳሰብ በአዲስና በተሻለ አስተሳሰብ መለወጥ ከዜጎች የሚጠበቅ ተግባር ነው። ያረጀውን ማደስ፣ የሌለውን ጥበብ መፍጠር፣ ያልነበረውን መልካም ተሞክሮ መቅሰም ከተማረ ትውልድ የሚጠበቅ ልዩ ተግባር ነው። በዘመን ሂደት፣ በትውልድ ቅብብል የማይጠቅምን ፖለቲካ ማራመድ ለፖለቲከኛውም፣ ለሕዝቡም ለአገሪቷም የሚያመጣው በጎ ነገር የለውም።

በመሆኑም ለአንድ መከላከያ እውን መሆን ካለው ሁለንተናዊ ትርፍ አንፃር ሕዝቡ ከመንግሥት ጎን ሊሆን ይገባል። ቆም ብሎ በማሰብ አላስፈላጊ የሆነውን መንገድ ከመከተል ሊቆጠብም ይገባል። የGestalt Psychology አስተምሮ «The whole is greater than the sum of each parts » እንደሚለው የአንድን ነገር ገጽታ የምንገነዘበው በጥቅል ውቅሩ እንጂ በነጠላ ይዘቱ አይደለምና ነጠላ አተያይና ፍርድን ማስወገድና ከመፍረድ በፊት ሙሉ ምስልን መመልከት መልመድ ይገባል።

መንግሥትም እያንዳንዱን ውሳኔና አፈፃፀሙን በየጊዜው ለሕዝብ ማሳወቅ መፈተሽን ሊዘነጋው አይገባም። የደህንነት ስጋት ባለባቸው አካባቢዎችና ክልሎችም መንግሥት አስተማማኝ የመከላከያ ሰራዊቱን በአግባቡ ማስፈር ግድ ይለዋል። ምክንያቱ ደግሞ በአንዳንድ አካባቢዎች ውሳኔን ለመቀበል ዳተኝነት የሚታየው ከደህንነት ስጋት ነውና።

የክልሎች የጸጥታ ኃይልም ለውሳኔው ውጤታማ ተግባራት ከመንግሥትና ከመከላከያ ጎን መቆም ይኖርበታል። ፖለቲከኞችም ሆነ አክቲቪስቶችም በውሸት ትርክት የራሳቸውን ድብቅ አላማ ለማሳካት ከመትጋት ይልቅ አላማውን በቀና መልኩ ለመረዳት መሞከርና አማራጭ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ከዚህ ባለፈ ካለ በቂ እውቀትና በአግባቡ ካለመረዳት በመከላከያው ሥራ እየገቡ ውዥንብር በመፍጠር በጉልበትና በአመፅ ከቀውስ ለማትረፍ ከመትጋት ሊቆጠቡ ይገባል።

መታወቅ ያለበት አብይ ጉዳይ ቢኖር ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹሙ እንዳሉት፣ ዘርን መነሻ አድርጎ በጉልበት ስልጣን እይዛለሁ፤ መንገድ በመዝጋት ስልጣን እይዛለሁ፤ ሕዝብን በማሳመፅ ስልጣን እይዛለሁ፤ አሁን ላይ አይሰራም። በፍፁምም አይፈቀድም። ስልጣን ለመያዝ የሚፈቀደውም አንድና አንድ መንገድ ብቻ ነው፤ ይኸውም የኢትዮጵያ ውስጥ ይመራኛል ያለውን 11 ሰዓት ተሰልፎ እንደመረጠ ጊዜው ሲደርስ 11 ሰዓት ድረስ ተሰልፎ ማውረድ ብቻ ነው። አንድን መንግሥት ማውጣትም ማውረድም የሚቻለው ሕዝብ ብቻ ነው። ከዚህ ውጪ ስልጣን በጉልበት አይገኝም።

> የኢትዮጵያ ሕዝብ ማወቅ ያለበት በአገሪቷ የፀጥታ ኃይል እንዲገነባ የሚፈቅደው ሕግ መንግሥት መከላከያና ፌዴራል ፖሊስን ነው:: ከመከላከያ ውጪ የታጠቀ ኃይል ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር የለበትም:: የታጠቀ ኃይል ሕግ የሚፈቅደው መከላከያ እና የብሔራዊ ደህንነቱ ነው

# “ዎገና” - የሀዲያ ብሄር ከብቶች የማስቆጠር ስነስርዓት

መላኩ ኤርሴ

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሄሮችና ብሄረሰቦች መገኛ ናት። እነዚህ ብሄሮችና ብሄረሰቦች በርካታ ሀገር በቀል ባህሎች፣ እውቀቶች እና ስርዓቶች ያላቸው እንደመሆናቸው ሀገሪቱም አያሌ ባህሎች፣ እውቀቶችና ስርአቶች ይገኙበታል።

እያንዳንዱን ብሄረሰብ ብንመለከትም እንዲሁ በርካታ ባህሎች፣ ስርአቶችና ሀገር በቀል እውቀቶች አሉት። የሀዲያ ብሄር ቱባ ባህል፣ ስርአትና ሀገር በቀል እውቀት ካላቸው ብሄረሰቦች አንዱ ነው። ከብሄረሰቡ ባህላዊ ስርዓቶች መካከል “ዎገና” የተሰኘው ባህል ይጠቀሳል። ዎገና የሀዲያ ብሄረሰብ ከብት የማስቆጠር ስርዓት ነው። በዛሬው ሀገርኛ አምዳችንም የዎገና ስርዓት ምንነትን፣ የስርዓቱን አፈጻጸም እንዲሁም ፋይዳውን እንዳስሳለን።

አቶ ካሳሁን አባይነህ በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር የትምህርት መርሃ ግብር ሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት “ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ዎገና) ስርዓት ክዋኔ በሀዲያ ብሄር” በሚል ርዕስ በሰሩት ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ እንደጠቀሰው፤ “ዎገና” ማለት አንድ ከብት አርቢ ከብቶቹ ከመቶ በላይ ወይም ከሺህ በላይ ሲሆኑለት ድግስ በመደገስ ሰዎች አውቀውለት ከሀብቱ ጋር በተያያዘ የክብር ማዕረግ ስያሜ የሚያገኝበትና የሚረጋገጥበት ስርዓት ነው።

በዎገና ዙሪያ የሚያጠነጥን መጽሃፍ በመጻፍ ላይ የሚገኙት አንትሮፖሎጂስት ተፈራ ጋቦሬ እንደሚሉት ደግሞ፤ “ዎገና” “ዎኦ” እና “ገና” የሚሉ ሁለት የሀዲይሳ ቃላት ተጣምረው የፈጠሩት ቃል ሲሆን፤ “ዎኦ” ውሃ ሲሆን “ገና” መርጨት የሚል ትርጉም አለው።

ስለዚህ ዎገና ማለት ከብቶች ላይ ውሃ፣ ማር እና ወተት በጥብጦ በእርጥብ ሳር እየነከሩ የመርጨት ስነ ስርዓት ነው። ዎገና ስርዓት በሁለት ይከፈላል፤ የከብት ብዛት ከአንድ መቶ በላይ ሲደርስ የሚፈጸመው ስርዓት “ጢቤ ዎገና” ሲባል፤ ከሺህ በላይ ሲደርስ የሚፈጸመው ደግሞ “ኩማ ዎገና” ይሰኛል። ከ100 በላይ ያስቆጠረው አርቢ “ጢባሞ” ሲባል፤ ከአንድ ሺህ በላይ ያስቆጠረው አርቢ ደግሞ “ኩማሞ” ተብሎ ይጠራል።

አንድ ከብት አርቢ ዎገና ስርዓት ለመድረስ ከ20 እስከ 40 ዓመት እንደሚፈጅበት የሚናገሩት አቶ ተፈራ ጋቦሬ፤ የዎገና ስርዓትን ለመፈጸም ቅድመ ሁኔታዎች እንዳሉ ይገልጻሉ። የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ አንድ ከብት አርቢ ያረባቸው ከብቶች ቁጥር ከ100 በላይ መድረስ አለበት። ይሁንና የከብቶቹ ቁጥር ከመቶ ስለተሻገረ ብቻ “የዎገና” ስርዓትን ማዘጋጀት አይችልም። የከብቶቹ ቁጥር መቶ እና ከዚያ በላይ መድረሱን በሚያረጋግጡት በ“መሃራኖ” መረጋገጥ አለበት።

“መሃራኖ” ማለት ከዚህ ቀደም ከ100 በላይ ከብት ያስቆጠሩ ከብት አርቢዎች ማህበር ነው። እንደ አቶ ተፈራ ማብራሪያ በሀዲያ ዞን ውስጥ በአሁኑ ወቅት ከ800 በላይ የሚሆኑ መሃራኖ በህይወት አሉ። እነዚህ “መሃራኖ” በሶስት ማህበር ተደራጅተው ይገኛሉ።

እንደ አቶ ተፈራ ማብራሪያ ፤ ከዚህ ቀደም ስርዓቱን ያስፈጸሙት መሃራኖ የአርቢው ከብት ለዎገና ስርዓት ደርሷል ወይ የሚለውን የማጣራት ስራ ይሰራሉ። የማጣራት ስራውን በግልጽ እና በስውር ያከናውናሉ። ከብቶቹን ገዝቶ ነው ወይስ ራሱ አርብቶ ነው፤ ምንጩ ከየት ነው? የሚለውን የማጣራት ስራ ይሰራሉ። ራሱ አርብቶ መቶ እና ከዚያ በላይ ያደረሰ ካልሆነ ስርዓቱ አይፈጸምለትም።

አጣሪዎቹ የከብቶቹን ቁጥርና የአረባብ ሂደቱን ካጣሩ በኋላ የዎገና ስርዓት ለማካሄድ መሟላት ያለባቸው ሌሎች ነገሮችንም ያጣራሉ። ከሚያጣሯቸው ነገሮች መካከል ከከብቶች እርባታ ጎን ለጎን በእርሻ ስራው ያለው እንቅስቃሴና የጓሮ አያያዝ፣ የሚኖርበት ቤትና የቤቱ ግቢ ሁኔታ፣ በደጁ ላይ ጥላ የተከለ መሆን አለመሆኑ፣ በምግብ ራሱን የቻለ መሆኑ፣ እሱ እና ባለቤቱ ለጉዞ የሚጠቀሙባቸው በቅሎና ፈረስ እንዳለውና እንደሌለው ያረጋግጣሉ።

የማጣራት ስራው እላይ በተጠቀሱት ብቻ



በሀዲያ ዞን ጎንቦራ ወረዳ ጎርጣ ቀበሌ ባለፈው ዓመት የዎገና ስርዓት በተካሄደበት ወቅት፤

አያበቃም። እጩ መሃራንኞና ቤተሰቡ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ያለው መስተጋብርም ይጣራል። እጩ መሃራንኞ እና ባለቤቱ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ያላቸው መስተጋብር፣ በማህበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ንቁ ተሳትፎ፣ ሀቀኝነታቸው፣ አስታራቂነታቸው፣ የተቸገረን የመርዳት ሁኔታቸው፣ ወዘተ ምን እንደሚመስል የአካባቢውን ማህበረሰብ በመጠየቅ ያጣራሉ።፡ እነዚህን ነገሮች ከተረጋገጡ በኋላ አርቢው የዎገና ስርዓት ለማዘጋጀት ብቁ መሆኑ ሲረጋገጥ የዎገና ስርዓት እንዲያዘጋጅ ይሁንታ ይሰጠዋል።

በደጋ አካባቢ የግጦሽ መሬት እጥረት ያለ ሲሆን አርቢዎቹ አብዛኛውን ጊዜ ከብቶቻቸውን ይዘው የሚያሳልፉት በዞኑ ውስጥ እና በአጉራባች ዞኖች ውስጥ በሚገኙ ቆላማ አካባቢዎች ነው። የወገና ስርዓት ለመፈጸም ይሁንታ ሲያገኙ ለከብቶቹ በረት በማዘጋጀት ከቆላማ አካባቢዎች ወደ ደጋ እንደሚያመጡ አቶ ተፈራ አብራርተዋል። ከብቶቹ ከቆላ አካባቢ ወደ ደጋ ከተመለሰ በኋላ ድግሱ ይጀመራል። ከሳምንት በኋላ ስርዓቱ ይፈጸማል።

እንደ አንትሮፖሎጂስት ተፈራ ገለጻ፤ በወግና ስርዓቱ ላይ በቅርብ እና በሩቅ የሚገኙ የሁሉም ቤተሰቦች ይሳተፋሉ። ስርዓቱ ላይ የሚሳተፉ፣ ስርዓቱን የሚፈጽሙትና ቤተዘመዶች በዋዜማው ይመጣሉ። ቤተዘመዶች እና ተጋባዝ እንግዶች በቡድን በቡድን እየሆኑ ሲመጡ የደስታ መግለጫ የሚሆኑ የተለያዩ ስጦታዎችን ይዘው ይመጣሉ። ያልተኮላሸ በሬ፣ ማር፣ ቅቤ፣ወጪታ ይዘው እየጨፈሩ እና ጡሩንባ እየነፉ ወደ ስፍራው የሚሄዱት።

ሁሉም በቡድን በቡድን ይዘው የመጡትን በሬ ለሰውዬው ካስረከቡ በኋላ ይመርቃሉ። ከዚያም በሬውን በማረድ የተወሰነውን ብልት እጩ መሃራንኞ ቤት በማስገባት የተቀረውን ደግሞ ወደተዘጋጀላቸው ድንኳን ይዘው ይሄዳሉ። የመጣው ቡድን ራሱን እያስተናገደ ይበላል፤ይጠጣል። ሌሊቱን የተለያዩ ጭፈራዎች ይደረጋሉ። ከዚህ ቀደም ከብቶቻቸውን ያስቆጠሩ መሃራኖ በእለቱ ከሌሎች ሰዎች ጋር አይገናኙም። ለብቻቸው አንድ ቤት ውስጥ ነው የሚሆኑት።

የወገና ስርዓቱ የሚካሄደው ንጋት ላይ ነው። ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ ቤተዘመዶች እየጨፈሩ ከብቶችን እየነዱ ወደ ወንዝ እንደሚሄዱ የጠቆሙት አንትሮፖሊጂስት ተፈራ፤ ወንዙ ዓመቱን ሙሉ የማይቋረጥ መሆኑን በቅድሚያ የማረጋገጥ ስራ እንደሚሰራም ጠቁመዋል።

ከብቶቹ ወንዙን ከመሻገራቸው በፊት ሰውም ሆነ የሌሎች ሰዎች እንስሳት እንዲያቋርጧቸው አይፈቀድም። የዎገና ስርዓት ሳይካሄድ ወንዙን ሌላ ሰው ወይም የሌላ ሰው እንስሳ ከተሸገረ የሰውዬው ሀብት ላይ ጥላ ያጠላበታል ተብሎ ይታሰባል። ወንዙን ቀድሞ የተሻገረ ሰው ሀብቱን ይዞ ይሄዳል ተብሎ ይታሰባል። የዚያን ሌሊት ከተቻለ አውሬዎች እንኳ ወንዙን እንዳይሻገሩ ቤተሰቡ መከላከል ይኖርበታል ይላሉ።

አንትሮፖሎጂስት ተፈራ እንዳሚናገሩት፤ ዋናው የወገና ስርዓት በሚካሄድበት ዕለት ንጋት ላይ የቤቱ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ አንድ ጥጃ ተሸክሞ ከከብቶች በረት ይወጣል። ጥጃውን ይዞ ሲወጣ ከብቶች ተከትለውት ከበረት ይወጣሉ። ጥጃውን የያዘው ልጅም ወደ ወንዙ ይሄዳል። እጩ መሃራንኞ እና ሚስቱም ወደ ወንዝ ይሄዳሉ። ወደ ወንዙ ሲሄዱ ዘመድ አዝማድ ከቧቸው ይጨፍራል ይሸልላል፣ ያቅራራል። ከብቶቹ ወደ ወንዙ ገብተው ወንዙን ሲሻገሩ ባል እና ሚስቱ ውሃ ውስጥ ቆመው ውሃ፣ ማር እና ቅቤ የተቀላቀለበት ፈሳሽ ከብቶች ላይ ይረጫሉ። ስርዓቱ ሲከወን እልልታውና ድራንቻ ይቀጥላል።

ወንዝ ላይ የሚካሄደው የዎገና ስርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ልክ ወደ ወንዙ ሲኬድ እንደተደረገው ሁሉ ባልና ሚስቱን አጅቦ ጭፈራ፣ ሸለላ እና ቀረርቶ ይደረጋል። ከወንዝ ወደ ቤት ሲመለሱ “መሃር እዮና” የሚል እና “ሽምበለለዮኒሄ” የሚሉ ባህላዊ ጭፈራዎች ይጨፈራሉ። “መሃር እዮና” ማለት ሹምት ይስማማህ፤ ወይም ሹመት ያዳብር የሚል ትርጉም ሲኖረው፤ “ሽምበለለዮኒሄ” ማለት ደግሞ ሁሉ ሞልቶ፣ ሁሉ ተትረፍርፎ ማለት ነው።

ስርዓቱ ከወንዝ መልስ ቤት ውስጥም ይቀጥላል። ከወንዝ መልስ ባልና ሚስቱ እቤት መሶሶ ስር እንዲቀመጡ ይደረጋል። አባዎራውና ባለቤቱ መሰሶ ስር ከተቀመጡ በኋላ ከዚህ ቀደም ክብት ያስቆጠሩ መሃራኖ እና አበጋዙዋ ወደ ቤቱ ይገባሉ። መሃራኖ እና አበጋዙዋ ቦታቸውን ከያዙ በኋላ አንድ ወይፈን ይቀርብላቸዋል። ከሰውዬው ጎሳ የተመረጡ ሽማግሌ በወይፈኑ ጀርባ ላይ ለምለም እርጥብ ሳር በማድረግ ይመርቃሉ። ምርቃቱ ከተካሄደ በኋላ ወይፈኑ ይታረዳል። ከታረደ በኋላ ነፍሱ ሳትወጣ የወይፈኑ “ሀንጩፋ” (የመራቢያ አካል) ተቆርጦ ይወጣል።

አቶ ተፈራ እንዳሉት፤ ከወይፈኑ ስጋ ክትፎ ተዘጋጅቶ፣ ቅቤ በብዛት እየተጨመረበት አበጋዞች እና መሃራኖ ይበላሉ። ማር እና ብርዝ ይቀርብላቸዋል። አስቆጣሪዎቹ ባልና ሚስቱም ይስተናገዳሉ። በልተው ጠጥተው ከጠገቡ በኋላ ስርዓቱን ይፈጽማሉ።

ስርዓቱን የሚፈጽሙት በፊት ማዕረጉን የተቀበሉ አበጋዙዋና መሃራኖ ናቸው። እነዚህ መሃራኖ ስርዓቱን ለመፈጸም ከታረደው ወይፈን “ደልቾ” (ሻኛ)፣ “ኤድራሳ” (ፍሪምባ)፣ “ሚዳዶ” (ጎድን)፣ “ሀንጩፋ” (የዘር መተላለፊያ) ይቀርብላቸዋል። እነዚህን ወደ አስቆጣሪው እና ባለቤቱ ይዘው ይቀርቡና በቅድሚያ ለአስቆጣሪው ደልቾ በጥርስ ያስነክሱና በቢላ ይቆርጣሉ። በመቀጠል ኤድራሳ በመቀጠል ደግሞ ሚዳዶ ያስነክሱና በቢላ ይቆርጣሉ። ከዚያ በመቀጠል ለሚስቱም በተመሳሳይ በጥርሷ በማስነከስ ይቆርጣሉ። በማስከተልም ሀንጩፋውን በአስቆጣሪው ቀኝ እጅ ላይ ያስገባሉ። የሚስቱ ደረት ላይ ደግሞ ከወይፈኑ ሆድ እቃ የተወሰደ ሞራ ይለጥፋሉ። በመጨረሻም ስርዓቱን ያስፈጸሙት መሃራኖ እና አበጋዞች አስቆጣሪውን መሃራንች ጢባሞ ወይም አበጋዝ ጢባሞ ብለው ይሰይሙታል። ሚስቱን ደግሞ “ጊፍቴ” ይሏታል።

የስርዓቱ ፈጻሚዎች ስርዓቱን ሲያከናወኑ መሃር እዮና እና ሻዕሞና እያሉ ሲሆን፤ “መሃር እዮና” ማለት ሹመት ያዳብር እንደማለት ነው፤ “ሻዕሞና” ማለት ደግሞ ይቅናህ ክብር አይለይህ ማለት ነው።

መሃራኖ እና አበጋዞች ስርዓቱን ከፈጸሙ በኋላ ተጠርተው የመጡ ቤተዘመዶችም ልክ እንደ መሃራኖ ሁሉ እንደ አመጣጣቸው በቡድን በቡድን በመሆን ስርዓቱን ይፈጽማሉ። ይዘው የመጡት ማር፣ ቅቤ እንዲሁም በዋዜማ ይዘው መጥተው ያረዱት በሬ ሻኛ፣ ፍርምባ እና ጎድን ይዘው በመምጣት መሃር እዮና እና ሽምበለለዮኒሄ እየጨፈሩ ስርዓቱን ይፈጽማሉ።

ይህም የሚደረገው መሃራኖ እና አበጋዙዋ ለአዲሱ አስቆጣሪው የሰጡትን ሹመት ማጽደቃቸውን ማረጋገጫ ነው። የወገና ስርዓት ተፈጽሞለት እውቅና ያገኘ ሰው በብሄሩ ይከበራል። ስብሰባዎችን በምርቃት ይከፍታል።

አቶ ካሳሁን አባይነህ ሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት “ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ዎገና) ስርዓት ክዋኔ በሀዲያ ብሄር” በሚል ርዕስ በሰራው ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ እንደጠቀሰው፤ በመጨረሻም “ወበጣ” አስቆጣሪውን እና ሚስቱን ገላ የማጠብ ስርዓት ይፈጸማል። ገላ የማጠቡን ስራ የሚሰሩት ቅርብ ቤተሰብ ናቸው። የወበጣ ስርዓት የሚፈጸመው አስቆጣሪው ወገና ስርዓት ለመፈጸም መንቀሳቀስ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ስርዓቱ እስከተፈጸመበት ባሉ ጊዜያት ካጋጠሙ ችግሮች ለማንጻት ነው።

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የሀገር በቀል እውቀት ጥናት ተቋም ዳይሬክተር አቶ እያሱ ጥላሁን እንደሚሉት፤ የዎገና ስርዓት ሰው ጠንክሮ ከሰራ ከምንም ተነስቶ ባለመቶ ከብት መሆን እንደሚችል ማሳያ ነው። ዎገና ሀብት እንዴት ማፍራት እንደሚቻል ያሳያል። ከብት ከሚያስቆጥሩት ኢንተርፕሪነርሽፕን መማር ይቻላል። በሀዲያ አከባቢ ያላቸውን አነስተኛ መሬት ተጥቅመው እጥረት አለብኝ ብለው ሳይቀመጡ ሀብት ማፍራት መቻላቸው ጥንካሬያቸውን ያመለክታል።

ከብት አርቢዎች በሀዲያ ዞን ውስጥ ባለው የመሬት ጥበት ምክንያት ወደ አጎራባች ዞኖች በመሄድ ከብቶቻቸውን እንደሚያረቡ የሚጠቅሱት አቶ ኢያሱ፤ በተለይም ጊቤ ወንዝን ተሸግረው ወደ ጅማ፣ ወደ ዳውሮ በመሄድ ከብቶቻቸውን እንደሚያረቡ ይናገራሉ። አንዳንዶች ከብቶቻቸውን ይዘው እስከ ጋምቤላ እንደሚሄዱ በመጠቆም በተለይም ሰፊ መሬት እና ውሃ ወዳለባቸው አጎራባች አካባቢዎች በመሄድ በሰላማዊ መንገድ የተፈጥሮ ሀብትን በመጋራት ከብቶችን የሚያረቡበት እውቀት የሚደነቅ ነው ይላሉ። የተፈጥሮ ሀብትን ብቻ ሳይሆን ከብቶቹን እና ከከብቶቹ የሚገኘውን ተዋጽኦ ከአከባቢው ማህበረሰብ ጋር የሚጋሩበት መንገድ የሚበረታታ መሆኑንም በመጥቀስ፣ እነዚህ ከብት አርቢዎች ከአካባቢው አልፎ ለመሃል ሀገር ሰንጋዎችንም እንደሚያቀርቡ ይናገራሉ።

እንደ አቶ ኢያሱ ማብራሪያ፤ ከብት አርቢዎቹ ለሀገር ኢኮኖሚ እያበረከቱት ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም፣ ለከብት አርቢዎቹ የተሰጠው ትኩረት እጅግ አነስተኛ ነው። በተለያዩ ጊዜያት በሚከሰት በሽታ ምክንያት ከብቶች ይሞታሉ። ባለ መቶ የነበሩ ሰዎች በአንዴ ባዶ እጃቸውን የሚቀሩበት ሁኔታ ያጋጥማል፤ መድሃኒት አይቀርብላቸውም። በመሆኑም መንግስት ለእነዚህ ከብት አርቢዎች ትኩረት መስጠት አለበት፤ መድሃኒቶችን ማቅረብ አለበት። አብዛኞቹ አርቢዎች ባሉባቸው የጊቤ በረሃ አካባቢዎች የመድሃኒት ማዕከላት ሊገነቡም ይገባል።

ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የአርብቶ አደሮቹን ችግር ለመፍታት ጥረት እያደረገ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ኢያሱ፣ የአከባቢውን ከብቶች ዝርያ በዘመናዊ ዝርያዎች ለመተካት እና አርቢዎቹ ብዙ ሳይንከራተቱ ምርትና ምርታማነታቸውን ከፍ ማድረግ እንዲችሉ በትኩረት እየሰራ መሆኑን ይገልጻሉ። ዩኒቨርሲቲው የከብት እርባታ ማዕከል በማዘጋጀት የወተት እና ስጋ መጠናቸው ከፍ ያሉ ዝርያዎችን ለማበራከት ጥረት እያደረገ እንደሆነም ተናግረው፣ ዩኒቨርሲቲው የኮርማ አገልግሎት በመስጠት የተሻሻለ ዝርያ ለማሰራጨት ጥረት እያደረገ ነው ብለዋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ብሎኬት አምራቹ ኢንጅነር

ማህሌት አብዱል

ወጣት ዘለቀ ተስፋ ይባላል፡፡ ትውልዱም ሆነ እድገቱ ከባህርዳር ከተማ ወጣ ብላ በምትገኘው ጎንጅ ቆለላ ወረዳ ቅዱስ ገብርኤል ቀበሌ ወሸራ ማርያም በምትባል አካባቢ ነው፡፡ በትምህርታቸው ጎበዝ ከሚባሉ ተማሪዎች መካከል እንደነበረ የሚናገረው ወጣቱ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሲገባ ህክምና የማጥናት ህልም እንደነበረው ያነሳል፡፡ ይሁንና የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ውጤቱ ጥሩ የሚባል ቢሆንም ህክምና ማጥናት የማያስችል በመሆኑ የሚወዳቸውን ፊዚክስና ማትስ ትምህርቶች የበለጠ ተግባራዊ ሊያደርግበት በሚችልበት ዘርፍ መርጦ አዳማ ዩኒቨርሲቲ አመለከተ፡፡ እናም ጥያቄው ተቀባይነት አግኝቶ ከአዳማ ዩኒቨርሲቲ በሜካኒካል ኢንጅነሪንግ ትምህርት ክፍል ገብቶ በ2013 ዓ.ም ተመረቀ፡፡ ዩኒቨርሲቲ ቆይታው ከጠበቀው በላይ ጥሩ የሚባል እንደነበር የሚያወሳው ይህ ወጣት በተለይ እንደእሱ አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችን የመስራት ተሰጥኦና ተነሳሽነት ያላቸውን ተማሪዎች በማበረታት ረገድ ይደረግላቸው የነበረው ድጋፍ የሚደነቅ እንደነበረ ያነሳል፡፡

ከእነዚህም መካከል ዩኒቨርስቲው ከጂአይዜድ ጋር በመተባበር ያዘጋጀው የፈጠራ ሥራ ውድድር አንዱ መሆኑን ጠቅሶ፤ በውድድሩ ላይም ማጨጃ ማሽን በመስራት ከተመረጡ ተፎካካሪዎች መካከል ሰባተኛ ደረጃን በመያዝ እውቅና አግኝቷል፡፡ ከተመረቀ በኋላ ግን በተማረበት የሙያ ዘርፍ እንዳሰበው ቶሎ ሥራ ማግኘት አልቻለም፡፡ የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ቢያመለክትም በለስ አልቀናውም፡፡ በዚህ ግን ተስፋ አልቆረጠም፤ በሙያው ሥራ እስከሚያገኝ ድረስ በሚል አዲስ አበባ በራይድ ሹፌርነት ተቀጥሮ ለአንድ ዓመት ያህል ሠራ፡፡

ይህ ግን ገቢ ከማግኘት ባሻገር ሕይወቱን የሚቀይር ሆኖ አላገኘውም፡፡ በመሆኑም ወደ ተወለደበት እና ያደገባት ባህር ዳር ከተማ በመመለስ ከአንድ ጓደኛው ጋር በመሆን የብሎኬት ማምረቻ ከፈተ፡፡ ወጣት ዘለቀ ከተማረበት ሙያ ውጪ ሥራ ለመጀመር ምክንያት የሆነውን ነገር ሲያነሳም ‹‹ዩኒቨርሲቲ በነበርንበት ወቅት የተለያዩ ስልጠናዎችን መውሰዴ በየትኛውም ዘርፍ ውጤታማ መሆን የምችልበትን ሥነ-ልቦና በማዳበሬ ነው›› ይላል፡፡ የከተማዋን ክፍተት አይቶ በዘርፉ ሥራ መጀመሩ ከወዲሁ ተስፋ ሰጪ ምልክቶች እንዳይ አድርጎኛልም ባይ ነው፡፡

ማምረቻ ቦታ ተከራይተው በ200 ሺ ብር ካፒታል መነሻ ብር በመያዝ እየሠራ መሆኑን የሚገልፀው ወጣት ዘለቀ፤ ግማሽ መንፈቀ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ምርታቸው ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ መምጣቱን ይገልፃል፡፡ በአሁኑ ወቅት በቀን 1ሺ 200 ብሎኬቶችን የማምረት አቅም ላይ መድረሳቸውንም ይናገራል፡፡ ‹‹ምንም እንኳን የኮንስራክሽን ሥራ እንደአገር ቢቀዛቀዝም የተሻለ ደንበኞችን የምንቀበልበት ሥርዓት በመፍጠር እና ከደንበኞች የምናገኘውን ምክረ ሃሳብ ላይ በመመርኮዝ ጥራት ያለው ምርት የምናመርት በመሆኑ ተቀባይነታችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው፤ አሁን ላይ ከነባሮቹ አምራቾች ባልተናነሰ ምርታችን ተፈላጊ እየሆነ ነው›› ሲልም አብራርቷል፡፡

በአሁኑ ወቅት ለዘጠኝ ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻላቸውን የሚገልፀው ወጣት ዘለቀ በተለይ የምርት ፍላጎት በሚጨምርበት ወቅት የተቀጣሪዎቹ ቁጥርም ከፍ እንደሚልም ያስረዳል፡፡ ወደፊት ከአነስተኛ የብሎኬት ማምረቻ ወደ ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የመሸጋገር አላማ ሰንቆ እየሠራ መሆኑን ይናገራል፡፡ በተለይም በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ኮንክሪት ማምረት ሥራ ለመግባት እቅድ ይዞ እየሠራ መሆኑን አመልክቶ፤ ጎን ለጎንም እንደእሱ በተለያዩ ሙያ ተመርቀው ሥራ ላጡ የከተማዋ ወጣቶች ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ፍላጎት ያለው መሆኑን ነው የጠቆመው፡፡ ከዚያ ባሻገርም በተመረቀበት ሙያ በተለይ በአግሮ ፕሮሰሲንግ ዘርፍ የሚሆኑ የማምረቻ መሣሪያዎችን ዲዛይን የሚያደርግ ኩባንያ ለመክፈትም ህልም እንዳለው አጫውቶናል፡፡



**ነገሮች የሚሳኩት መውደቅ የማንፈራ ከሆነ ነው፡፡ በተለይ ወጣት መቁረጥ የለበትም! ጤናም ጉልበትም እውቀትም የሚኖረው በወጣትነት ዕድሜ ስለሆነ መሮጥ ያለብን ይሄኔ ነው፡፡ ብንወድቅም ደግሞ ራሳችንን አንስተን ድጋሜ መሮጥ ነው እንጂ ተስፋ መቁረጥ በፍፁም አያስፈልግም፡፡ በቃ ሕይወት ይቀጥላል!**

ይሁንና በተለይ አሁን ካለው የዋጋ ንረት ጋር ተያይዞ የማምረቻ ግብዓቶች ዋጋ በየጊዜው የሚጨምር እና እንደልብ ለማግኘት አደጋች ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ወደ ኢንዱስትሪ የመሸጋገር ህልማቸው ላይ አሉታዊ የሆነ ጫና እንዳያሳድር ስጋት እንዳለው አልሸሸገም፡፡ ‹‹በየጊዜው እየናረ የመጣው የግብዓት ዋጋ እንዲሁም በምንፈልገው መጠን ባለማግኘታችን አሁን እንኳን በምናመርተው ምርት ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ ነው ያለው፤ ይህ ችግር በአፋጣኝ የሚወገድበት ሁኔታ ካልተፈጠረ ወደፊት ለያዝነው የማደግ ትልማችንም ስጋት ይሆንብናል የሚል ፍርሃት አለኝ›› ሲል ይገልፃል፡፡

ወጣት ዘለቀ እንደሚለው፤ የራስን ሥራ ፈጥሮ የራስን የገቢ ምንጭ ማሳደግም ሆነ ለአገር ረብ ያለው ሥራ ከመሥራት አኳያ ወጣቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ የቁርጠኝነት ችግር ይስተዋላል፡፡ ሁሉ ነገር ተመቻችቶላቸው እና ተደራጅተው ሥራ የጀመሩትም ቢሆኑ በአገሪቱ ከሚፈጠረው ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር ጋር ተያይዞ ቶሎ ተስፋ የመቁረጥ ነገር ይታያል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የራሳቸውንም ሆነ ውጫዊ ተግዳሮቶችን ሰብረው ማለፍ የቻሉ ወጣቶችን የሚያበረታታ ሥርዓት አለመኖሩ የሥራ ፈጣሪዎች ቁጥር በሚፈለገው ደረጃ እንዳያድግ አድርጎታል፡፡

በዋናነትም በየመንግሥት ተቋማቱ ያለው ኋላቀር ሥርዓትና በቢሮክራሲ የታጠረ አገልግሎት ተጠቃሽ ችግር መሆኑን ያነሳል፡፡ ወጣቶች የሥራ እቅድ ወይም ፕሮጀክት ይዘው በሚመጡበት ጊዜ የንግድ ፍቃድ ፤ የፋይናንስ እና የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት ረገድ ሰፊ ክፍተት መኖሩን ይናገራል፡፡ የራሱን ተሞክሮ በማንሳት ‹‹እኔ ይህንን ሥራ ለመጀመር የንግድ ፍቃድ ለማውጣት ብቻ ሦስት ወር ነው የፈጀብኝ›› ይላል፡፡ ይህም ባሰበው ጊዜ ሥራውን እንዳይጀምር ያደረገው መሆኑንና ለተጨማሪ ወጪ የዳረገው መሆኑን ያመለክታል፡፡

እነዚህን ሁሉ ውጣ ውረዶች አልፎ ሥራ ቢጀምርም የማምረቻ ቦታ በማግኘት እንዲሁም ደግሞ የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው በማገዝ ረገድ በከተማ አስተዳደሩ የሚደረገው ድጋፍ እዚህ ግባ የሚባል እንዳልሆነ ነው ያነሳው፡፡ ‹‹ እኔ ሥራ ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ እዚህ እስከምደርስበት ድረስ የሥራ ሂደቴን መጥቶ ያየ፤ የሚጎድለኝን ጠይቆ ድጋፍ ያደረገልኝ አንድም የመንግሥት አካል የለም›› ይላል፡፡ ይልቁኑም በመንግሥት ተቋማቱ ያለው ውስብስብ እና ምቹ ያልሆነ አሠራር አምራቹን ተስፋ እያስቆረጠና ከሥራው እንዲወጣ የሚገፋፋ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከዚህም ባሻገር እንደማንኛውም ጀማሪ ሥራ ፈጣሪ ከባንኮች የብድር አቅርቦት ማግኘት ባለመቻላቸው እቅዳቸውን ባሰቡት ልክ ማሳካት እንዳላስቻላቸው ወጣት ዘለቀ ያነሳል፡፡ ‹‹የገንዘብ እጥረት ሁሌም ያለ ችግር ነው፡፡ አሁን ላይ በእጅ የሚቆይ ገንዘብ ባይኖርም የአንዱን ምርት ገቢ ለቀጣዩ መሥሪያ እንዲሆን እየተደረገ እንጂ ቢዝነስን ይዞ የሚያበድር አንድም ባንክ አላገኘሁም፡፡ የምናስይዘው ንብረት ከሌለን በቀር ከባንክ ብድር ማግኘት የማይታሰብ ነው›› ይላል፡፡ በተለይ ለሁለት ተደራጅተው ለሚሠሩ ወጣቶች ባንኮች የሚያበድሩበት ሥርዓት ያለመኖሩ እንደእሱ ሥራቸውን ማስፋፋት ለሚፈልጉ ሥራ ፈጣሪዎች ተስፋ አስቆራጭ እንደሆነባቸው ያመለክታል፡፡ እስካሁንም ሥራውን ማዝለቅ የቻለው እቁብ በመግባትና ከግለሰቦች በመበደር እንደሆነ ይጠቅሳል፡፡

ባንኮቻችን ቢዝነስን እንደ መያዣ አድርገው ማበደር ቢጀምሩ በጣም ጠቃሚ እንደሚሆንም ያመለክታል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ማሽን በበድር የሚገዙ ድርጅቶችን ማስፋፋት እንደሚገባ ይናገራል፡፡ ‹‹እኔ ለምሳሌ የመስሪያ ማሽኖችን የገዛሁት ዋሊያ ካፒታል ከሚባል የዕቃ ብድር ተቋም ነው፡፡ ግን ደግሞ እንደእኔ ይህንን ዕድል ያላገኙና ወደ ሥራ ያልገቡ ብዙ ወጣቶች አሉ፤ በመሆኑም እንዲህ ዓይነት አገልግሎት የሚሰጡ የብድርና ቁጠባ ተቋማትን ማስፋፋት ይገባል›› ሲል አመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ እንዲሁም የውሃ እጥረት ለሥራቸው መጓተት ዋናው ምክንያት እንደሆነባቸው ያነሳል፡፡ ‹‹የመብራት መቆራረጥ ምንም ሊያሠራን አልቻለም፤ በተለይ የመስሪያ ውሃ ማግኘት ትልቅ ፈተና ነው የሆነብን፡፡ በዚህ ምክንያት የአንድ ቀን ምርት ዋጋ ማጣት ማለት በጣም ከባድ ነው፡፡ በተዋዋልንበት ጊዜ ማድረስም ይጠበቅብናል፡፡ ባለን አቅም ደግሞ ውሃም ሆነ ለመብራቱ ጄነሬተር ተገዝቶ በየጊዜው ነዳጅ እየተሞላ የሚሠራው ሥራ ትርፋማ አያደርገንም፡፡ የቱንም ያህል ደንበኞች ብናፈራም የምንሠራው ሥራ ትርፉ ወጪ ከሆነ ሥራችን ቀጣይነት አይኖረውም›› ሲል አብራርቷል፡፡ በመሆኑም መንግሥት ይህንን ዓይነት የመሠረተ ልማት ፍላጎቶችን የማመቻቸት ኃላፊነቱን ሊወጣና የዘርፉን ተዋናዮች ሸክም ሊቀንስ እንደሚገባ ነው ያስገነዘበው፡፡

ዝግጅት ክፍላችንም የወጣቱን የሥራ ትጋትና ለመለወጥ ያለውን ትልም በማየት የሚመለከታቸው የሥራ አካላት በዘርፉ የሚነሱትን ቁልፍ ችግሮች ለመፍታት ቁርጠኛ መሆን እንዳለበት ማሳሰብ ይወዳል፡፡ በተለይ እንደወጣት ዘላቀ ዓይነት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው ሥራ ሳይንቁ ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች የተረፉ ወጣቶችን መደገፍ እና ማገዝ ይገባል የሚል መልዕክት ማስተላለፍ ይወዳል፡፡

‹‹እነዚህ ሁሉ ችግሮች ቢኖሩብኝም ፤ የሚያጋጥሙኝ ፈተናዎች በፅናት በማለፍ ለሌሎችም የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሌ ግን ከምንም በላይ ያስደስተኛል›› የሚለው ወጣት ዘለቀ፤ በተለይ እንደእሱ በተለያዩ ሙያዎች ሰልጥነው ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጡ ሥራአጥ ወጣቶች ከእሱ ተሞክሮ በመነሳት ሥራ ሳይንቁ ራሳቸውን ከጥገኝነት ሊያወጡ እንደሚገባቸው ይናገራል፡፡ በተለይ በተማሩበት ሙያ ብቻ ሥራ ለማግኘት በሚል ጊዜያቸውን በከንቱ እያቃጠሉ ያሉ ወጣቶች ያሉበት አገራዊ ነባራዊ ሁኔታ መረዳት እንደሚገባቸው፤ በአሁኑ ወቅት ምን ብሠራ ያወጣኛል የሚለውን ነገር ማጤንና አዋጭና ቶሎ ገቢ የሚያገኙበትን ዘርፍ መቀላቀል እንዳለባቸው ይመክራል፡፡

ነገሮች የሚሳኩት መውደቅ የማንፈራ ከሆነ ነው፡፡ በተለይ ወጣት መቁረጥ የለበትም ! ጤናም ጉልበትም እውቀትም የሚኖረው በወጣትነት ዕድሜ ስለሆነ መሮጥ ያለብን ይሄኔ ነው፡፡ ብንወድቅም ደግሞ ራሳችንን አንስተን ድጋሜ መሮጥ ነው እንጂ ተስፋ መቁረጥ በፍፁም አያስፈልግም፡፡ በቃ ሕይወት ይቀጥላል፡፡”

በዚህ ረገድ መንግሥትም እና የሚመለከታቸው አካላት አዳዲስ ምሩቃንንም ሆነ ሥራ ሳይንቁ ተደራጅተው መስራት የጀመሩ ወጣቶችን በተጨባጭ ውጤታማ ሊያደርጓቸው የሚችሉ ሥልጠናዎች በተከታታይነት የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር እንዳለባቸው ያስገነዝባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለመነሻ የሚሆን የፋይናንስ ድጋፍ፤ የማምረቻ ቦታ እና የገበያ ትስስር የሚፈጠርበት ሁኔታ ማመቻቸትም ወሳኝ መሆኑን ይገልፃል፡፡

# የምድር በረከት

# የጂኦሳይንስ ቤተ-ሙከራ የማእድን ዘርፉ ወሳኝ አቅም

**ስምስም መንግሥቱ**

ኢትዮጵያ በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የአስር አመቱ መሪ እቅድ የምጣኔ ሀብቱ ምሰሶ ብላ ከያዘቻቸው አምስት ዘርፎች መካከል ማእድን አንዱ ነው። ይህ ወሳኝ ዘርፍ ለልማቱ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን እንዲሁም ለልማቱ የሚያስፈልጉ እንደ ውጭ ምንዛሬ ያሉትን ሀብቶች ለማግኘት በእርግጥም ወሳኝ ነው።

በሌሎች ሀገሮችም ቢሆን ይህ ዘርፍ ወሳኝ ነው። ከዘርፉ የበለጠ ለመጠቀም ያደጉት ሀገሮች ሆኑ በሀገራቸው ያለውን ማእድን ከማልማት ጎን ለጎን የሌሎች ሀገሮችን ማእድን በማልማት ተጠቃሚ ለመሆን ዕርብርብ ያደርጋሉ። አንዳንዶቹ የሀገራቸውን የማእድን ሀብት አስቀምጠው የሌሎች ሀገሮችን ማዕድን ሲቀራመቱ ነው የሚታዩት።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የሀገሮችን የጥሬ እቃ ፍላጎት ከሚያሟሉ ግብአቶች ማዕድን በሁለተኛ ደረጃ ይይዛል። ዛሬ በስፋት የሚከናወነው የመሠረተ-ልማት ግንባታ እንዲሁም ለግንባታው ከሚውሉ ዋና ዋና ግብአቶች ሲሚንቶና ብረት ይጠቀሳሉ፤ ለትራንስፖርቱ ዘርፍና ለሀይል አማራጭነት ደግሞ ነዳጅ፣ የተፈጥሮ ጋዝና የድንጋይ ከሰል ይፈለጋሉ፤ የግብርና ምርትና ምርታማነት ሲታሰብ የአፈር ማዳበሪያ፣ ለእዚህ አገልግሎት የሚውሉ ፖታሽ፣ ፎስፌትን ጨምሮ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ግብዓቶች፣ ወዘተ ከተፈጥሮ ሃብት የሚገኙ ናቸው።ይህ እንግዲህ ጥሬ እቃ ብቻን የተመለከተ ነው። በዚህ ላይ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ በመሆን የሚያገለግሉ እንደ ወርቅ፣ ለጌጣጌጥ የሚውሉ የከበሩ ድንጋዮች፣ወዘተ የሚገኙት ከምድር ውስጥ ነው።

እነዚህን ማእድናት ገዝቶ መጠቀም በኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ፈተና ነው፤ ለማልማት ቴክኖሎጂ፣ የሰለጠነ የሰው ሀይል፤ ፋይናንስ፣ የመንግስት ቁርጠኛነት፣ አደረጃጀት ወሳኞቹ ናቸው። እንዲያም ሆኖ ግን ሀገሮች የአቅማቸውን ያህል ማእድናቱን ለማስጠናትና ለማልማት ጥረት ያደርጋሉ።

ወደ ዝርዝር ስንመጣ ደግሞ ለማዕድን ልማት ወሳኝ ከሆኑት መካከል በዘርፉ በሰለጠነ የሰው ኃይል፣በቴክኖሎጂ የተደራጀና የማዕድን ምርመራዎችና ትንታኔዎች የሚሰጥበት ቤተሙከራ (ላቦራቶሪ አንዱ መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ። ከምድር ተቆፍሮ የሚወጣው ማዕድን በውስጡ የያዛቸው ንጥረ ነገሮች፣ መጠናቸውና ጥራታቸው በቤተ ሙከራ (ላቦራቶሪ) በፍተሻ መለየትና መተንተን ይኖርበታል። በዚህ ሂደት ውስጥ ካላለፈ በዓለም ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ የሆነ ጥሬ ማዕድንና የማዕድን ውጤት ለማቅረብ እንደሚያስቸግር፣ በተመራጭነትና በተዓማኒነት ግብይቱ ላይ ጫና እንደሚፈጥር ባለሙያዎቹ ያስገነዝባሉ።

ሥነ ምድር የተመለከቱ ጥናታዊ ምርምሮችና መረጃዎችን የመሰብሰብና የመተንተን ስራ በቴክኖሎጂ የታገዘ መሆን ይኖርበታል። በዚህ መልኩ የተደራጀ ቤተ ሙከራ ማቋቋም ብቻውን በቂ እንዳልሆነም እንዲሁ ባለሙያዎቹ ይገልጻሉ። በላቦራቶሪ ውስጥ ያለፈ የማዕድን ፍተሻ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት የሚኖረው የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ISO accreditation) ሲኖረው እንደገባም ይጠቁማሉ።

ኢትዮጵያ ከምድር በረከት አንዱ የሆነው የማእድን ሀብቷ በኢኮኖሚው ውስጥ ላቅ ያለ ድርሻ እንዲኖረው ዘርፉ እንዲነቃቃ በአዲስ አደረጃጀት(ሪፎረም) መጠነሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ትገኛለች። ለማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚው ወሳኝ ለሆነው በቤተ-ሙከራ ውስጥ ለሚከናወነው የማዕድን ምርመራና ትንተና ስራ ትኩረት ሰጥታ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነችም ነው። በዚህ በኩል እየተደረገ ያለው ጥረትም ከዛሬ 50 ዓመት በፊት የተቋቋመውን የጂኦሳይንስ ላቦራቶሪ ዘመኑ ከሚጠይቀው አደረጃጀት ጋር እንዲራመድ በማድረግ የተሻለ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል ነው።

የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት የጂኦሳይንስ ቤተ-ሙከራ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ኢጃራ ተሰፋዬ ስለቤተ ሙከራው የእስካሁን እንቅስቃሴና በዘመናዊ አደረጃጀት የተሻለ ሥራ ለመሥራት እየተደረገ ስላለው ጥረት ሲገልጹ፣ በቅድሚያ በቤተ-ሙከራ ክፍሉ የሚከናወነው በመሬት ውስጥ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን መመርመርና መረጃዎችን ማመንጨት ነው ይላሉ።

ቤተ ሙከራው ሥራውን ለማከናወን የሚያስችሉ በውስጡ የተለያዩ አደረጃጀቶች ወይንም ክፍሎች አሉት። ክፍሎቹም የፊዚካልና ሚኖሮሎጂ፣ ጂኦኬሚካል፣ የሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ጥገና ክፍሎች ናቸው። ከነዚህ ውስጥም የጂኦኬሚካል ክፍል የድንጋይ ወይንም የአፈር (rock or soil) እና ተመሳሳይ የሆኑ ናሙናዎችን ይመረምራል። የሚከናወነው የምርመራ ሥራም ማዕድኑ በውስጡ የያዘውን ንጥረ ነገር ለመለየት ያስችላል።

ቢዘህ ክፍል በተጨማሪ የወርቅ ማዕድን ምርመራ ሥራ የሚከናወን ሲሆን፣ የወርቅ ጥራትና ካራት በምርመራ ይለበታል። ለምሳሌ ያህል በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ውክልና የተሰጠው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከወርቅ ማዕድን አምራቾች የሚረከበው ወርቅ በቤተ ሙከራ ፍተሻ ያለፈ መሆን ይኖርበታል።

የወርቅ ማዕድን ልማት በሚከናወንባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች የጥራት ምርመራን ተደራሽ ለማድረግ የምርመራ ላቦራቶሪ ማቋቋም ተችሏል። እነዚህ በየአካባቢው ተቋቁመው የምርመራ አገልግሎት የሚሰጡት ፍቃድ ካላቸው ባህላዊ የወርቅ አልሚዎች የሚቀርበውን የወርቅ ማዕድን ነው። ቤተ ሙከራውን ማደራጀቱንና ባለሙያዎችንም የማሟላቱ ሥራ የተከናወነው በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ነው። በየአካባቢው የሚከናወነው የወርቅ ምርመራ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ወርቁ ወደ ማዕከል መጥቶ ግዥው ይፈጸማል።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚቀርበውን የወርቅ ግዥ የሚፈጽመው በዚህ ሂደት ነው። የወርቅ ማዕድን ልማቱ በሚከናወንባቸው አካባቢዎች ላይ ምርመራ እንዲከናወንባቸው የተለዩት 13 ናቸው፤ ዋና ዋና ከሚባሉትም ኦሮሚያ ክልል ጉጂ፣ ሻኪሶ፤ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ ግልገል በለስ፣ ሲዳማ ክልል ሀዋሳ፣ ጋምቤላ ክልል ዲማ ይጠቀሳሉ። ከተለዩት 9ኙ በሥራ ላይ ናቸው። በትግራይ ክልል ሽሬ በአፋር ክልል ደግሞ ኮነባ በተባሉት አካባቢዎች በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ሲካሄድ በነበረው ጦርነት ሥራው ለጊዜው ተቋርጧል።

በቤተ-ሙከራው ስለሚደረግ የምርመራ ዘዴ አቶ ኢጃራ ለአብነት በወሰዱት አንድ ክፍል ተመስርተው ሲያስረዱ እንደገለፁት፤ ምርመራው ፊዚካልና ዲስትራክቲቭ ይባላል። ዲስትራክቭ የሚባለው የምርመራ ዘዴ የምርመራው ውጤት ከታወቀ በኃላ ለግብዓትነት ጥቅም ላይ የዋለው ናሙና መልሶ አይገኝም። «ነን ዲስትራክቲቭ» የሚባለው የምርመራ ዘዴ ደግሞ ምርመራው ከተካሄደ በኃላ ናሙናው ይኖራል። አብዛኛው ምርመራ ከተካሄደ በኋላ መጠኑ ቢለያይም ናሙናው የሚገኝ በዚህ ዘዴ ነው። የሳይንቲፊክ መሳሪያ ጥገና ክፍሉም ለምርመራ ክፍሉ እጅግ አጋዥ ነው።

የምድር ሀብቶች ወርቅና የከበሩ የጌጣጌጥ ማዕድናት ብቻ አይደሉም። እንደ ብረት፤ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ በመሳሰሉት ላይ በምን ሁኔታ ምርመራ እንደሚካሄድ አቶ ኢጃራ ጠይቀናቸው በሰጡት ምላሽ፣ በነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ላይም በተመሳሳይ ምርመራ የሚካሄድበት እድል ቢኖርም ለጊዜው በነዳጅ ላይ እየተሰራ አይደለም ሱሉ መለሱልን። ከነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ውጭ ባለው ላይ ምርመራ እንደሚከናወንና በአብዛኛው ደግሞ ከድንጋይ አለት፣ ከአፈር ጋር በተያያዙት ማዕድን ነክ በሆኑት ላይ ምርመራው እንደሚከናወን አስረድተዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የማዕድን ምርመራ ሥራ በመሰከም የተደገፈ ነው። ኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ግን አሁን እያከናወነ ባለው ተግባር ምርመራውን የሚያከናውነው የሚመጣለትን ናሙና በመመርመር ነው። በዚህም ተልእኮውን እየተወጣ ይገኛል። የመስክ የምርመራ ዘዴ ለምን እንደማይካሄድ ሲገልጹም አንዱ ክፍተት የማዕድን ልማቱ በሚከናወንበት ስፍራ ተገኝቶ ምርመራ ማከናወን አለመቻል እንደሆነ ነግረውናል። ይህን ማድረግ ያልተቻለው የአቅም ውስኑነት በመኖሩ መሆኑን ይገልጻሉ።

> **በዚህ ወቅት የማዕድን ምርመራ ፍላጎት ጨምሯል። ይህም ተደራሽነትን ማስፋት ይጠይቃል። አገልግሎቱም ቢሆን በዘርፉ በሰለጠነ የሰው ኃይል ዘመኑ በሚጠይቀው ቴክኖሎጂ መሰጠት ያለበት መሆኑ የግድ ነው። አሁን በተሻለ አደረጃጀት የተሻለ ሥራ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ ይገኛል**

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ የቤተ-ሙከራ ቁሳቁስ በግዥ ከውጭ የሚመጣ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የገንዘብ አቅም ይጠይቃል። በዘርፉም የሰለጠነ የሰው ኃይል ያስፈልጋል። ከመሳሪያው ጋር ለመተዋወቅም ስልጠናው በውጭ ሰዎች መሰጠት ይኖርበታል። ለቤተ-ሙከራ የሚሆን ህንጻ ግንባታን ለማከናወንም ከፍተኛ ወጪን ይጠይቃል። የማዕድን ልማቱ በሚከናወንባቸው አካባቢዎች በቁሳቁስ የተደራጀ ቤተ-ሙከራ ለማቋቋም ከፍተኛ በጀት ያስፈልጋል። አሁን ባለው አሰራር ከወርቅ ማዕድን ውጭ ያሉት ናሙናዎችን በማስመጣት ነው የምርመራ ሥራው የሚከናወነው ሲሉ ያብራራሉ።

"የቤተ ሙከራ ስራውን ተደራሽነትን ለማስፋት አቅም የሚጠይቅ ቢሆንም በዚሁ መቀጠሉ በዘርፉ የሚፈለገውን ውጤት የሚያስገኝ ባለመሆኑ የግዴታ ወደ ተግባር መግባት ያስፈልጋል" የሚሉት አቶ ኢጃራ፤ በቀጣይ የመስክ ምርመራ ለማድረግ የሚያስችል ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ እንደታሰበበትና የተጀማመሩ ሥራዎች መኖራቸውንም አመልክተዋል።

የማዕድን ዘርፉ በሀገር የምጣኔ ሀብት እድገት ውስጥ ሚና እንዲኖረው በሚደረገው ጥረት አሁን ባለው አሰራር የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት አቅሙ በምን ደረጃ ላይ ነው? የሚል ጥያቄ ያነሳንላቸው አቶ ኢጃራ፣ «በዚህ ወቅት የማዕድን ምርመራ ፍላጎት ጨምሯል። ይህም ተደራሽነትን ማስፋትን ይጠይቃል" በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል። አገልግሎቱም ቢሆን በዘርፉ በሰለጠነ የሰው ኃይል ዘመኑ በሚጠይቀው ቴክኖሎጂ መሰጠት ያለበት መሆኑ የግድ እንደሆነም ጠቅሰው፤ አሁን በተሻለ አደረጃጀት የተሻለ ሥራ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ይገልጻሉ።

ኢንስቲትዩቱ ለራሱ ተቋም ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ በማዕድን ልማት ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ ግለሰቦች፣ ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች ጥያቄ ሲያቀርቡ አገልግሎት እንደሚሰጥም ነው የተናገሩት። በህገወጥነት በሚያዙ ማእድናት ላይ የምርመራ ትእዛዝ ሲቀርብለትም መርምሮ መረጃውን እንደሚሰጥ ነው አቶ ኢጃራ ያስረዱት። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለጥናትና ምርምር ሲፈልጉም ኢንስቲትዩቱ ክፍት እንደሆነና ከዩኒቨርሲቲ ለተግባር ልምምድ የሚላኩትንም ተቀብሎ እንደሚያግዝ ገልጸዋል።

የቤተ-ሙከራው መኖር ወሳኝ ከሆነ በምን አቅም ነው መገንባት ያለበት የሚል ጥያቄም አቅርበንላቸው በሰጡት ምላሽ፤ ላቦራቶሪው በዘመናዊ ቁሳቁስና በሰለጠነ የሰው ኃይል ማደራጀት ወይንም ማሳደግ ግዴታ መሆኑን አስታውቀዋል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የላቦራቶሪው የምርመራ ውጤት ዓለም አቀፍ ተቀባይነት እንዲኖረው የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ISO accreditation) ሊኖረው ይገባል ይላሉ። እስከ አሁን ባለው አሰራር የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለመኖሩ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ላይ ጥያቄ የሚያስነሳበት ሁኔታ እንዳለ ጠቅሰው፣ አንዳንድ ደንበኞችም የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወዳላቸው ሀገሮች እንደሚሄዱም አመልክተዋል። አሁን ግን ክፍተቱን ለመሙላት ጥረቶች እየተደረጉ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ።

ከአቅም ማጎልበቻ ዘዴዎች አንዱ በዘርፉ ተሞክሮ ካላቸው ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በትብብር መሥራት ነው። በዚህ ትብብር ሀገር ውስጥም ወደ ውጭ ሀገር በመሄድም ተሞክሮ ለመቅሰም ጥረት ይደረጋል። በዚህ ረገድ ኢንስቲትዩቱ ያከናወናቸው ተግባሮች ስለመኖራቸው አቶ ኢጃራን ጠይቀናቸው በሰጡት ምላሽ ፣ ፕሮጀክቶች ተቀርጸው እንቅስቃሴ ሲኖር፣የሥራ መሣሪያ ድጋፍ እንደሚደረግ ፣በቅርቡም በማዕድን ሚኒስቴር አማካኝነት ከአንድ የካናዳ ፕሮጀክት ለላቦራቶሪ ሥራ የሚያግዝ የመሣሪያ ቁሳቁስ ድጋፍ መገኘቱን ገልጸዋል። በድጋፍ ከተገኙት መሣሪያዎች አብዛኛዎቹ ለከበሩ ማዕድናት ምርመራ የሚውሉ እንደሆኑም አመልክተዋል። እንዲህ አይነት ድጋፎች አልፎ አልፎ እንደሚገኙም ነው የጠቀሱት።

የጂኦሳይንስ ቤተ-ሙከራ በአፍሪካ ደረጃ በጥሩ አደረጃጀት የሚጠቀስ እንደነበርም አቶ ኢጃራ አስታውሰው፤ ከዚህ ቀደም በነበረው ስም መጓዝ ባለመቻሉ ነው በዚህ ወቅት ዘርፉ የሚፈለገውን ያህል መጓዝ ያልቻለው ይላሉ። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም ለዘርፉ ይሰጥ የነበረው ትኩረት አነስተኛ መሆን አንዱ ምክንያት መሆኑን ይገልጸሉ። በዚህ የተነሳም የተሻለ የደመወዝ ክፍያና ጥቅማጥቅ ፍለጋ የባለሙያዎች ፍልሰት መኖሩ ለመዳከሙ አንዱ ምክንያት መሆኑን ይጠቅሳሉ። ወቅቱን የሚጠይቅ ለምርመራ ሥራ የሚያግዝ መሳሪያ ግዥ አለመኖርም ሌላው ክፍተት እንደሆነ ነው የጠቆሙት።

"በአሁኑ ጊዜ በጂኦሳይንስ ቤተ-ሙከራ ውስጥ በአብዛኛው የሚያስፈልጉት ባለሙያዎች ኬሚስትና ጂኦሎጂስት ናቸው" የሚሉት አቶ ኢጃራ፣ በዚህ ዘርፍ የተመረቁ ባለሙያዎች ቅጥር እንደሚፈጸምም ነው የገለጹት። አዳዲስ ሙሩቃን ሲቀጠሩ ከሙያው ጋር እንዲተዋወቁና የተሻለ አፈጻጸም እንዲያሳዩ ተጨማሪ ስልጠና ለመስጠት አንድ ክፍል መደራጀቱንም ነግረውናል።

አቶ ኢጃራ እንደሚሉት፤ ጂኦሳይንስ ቤተ-ሙከራ መኖሩ ለማእድን ልማቱ መቀላጠፍ ወሳኝና አስፈላጊ ቢሆንም፣ በተሻለ አደረጃጀት ላይ መገኘት ይኖርበታል። ይህንንም በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለመፍታት በተለይም ዩኒቨርስቲዎች በሁለተኛ ዲግሪ ባለሙያዎችን እንዲያፈሩ ስምምነት ላይ በመደረሱ ወደ ትግበራ ተገብቷል። የውጭ ስልጠናም ጎን ለጎን እንዲመቻች ጥረት እየተደረገ ነው።

ቤተ-ሙከራው በተሻለ አገልግሎት እንዲሰጥ አሁን ካለበት በተሻለ የህንፃ ግንባታ እንዲከናወን በእቅድ መያዙንም ጠቅሰው፣ በረጅም ጊዜ እነዚህን እቅዶች በማሳካት አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ እንደታሰበ ጠቁመዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የንጋት ዜማ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

ገና እየነጋ ነው..ሁለት ዓይነት የብርሃን ቀለም በበሯ ሽንቁር ይታያታል። በመኝታዋ ግርጌ ካለው የግራር ዛፍ ላይ ወፎች ሲንጫጩ ይሰማታል። የጎረቤቷ የእማማ ስህን አውራ ዶሮ በማን አለብኝነት ሲያንቃርር ይሄም ይሰማታል። ማለዳዋ እንዲህ ነው በወፎች ንትርክና በአውራ ዶሮ ድንፋታ የተሞላ። ባልመሸና ባልነጋ ሁለት ዓይነት ዓለም ውስጥ ሆና ስለ ነገ የምትጨነቅ።

ማለዳ ትወዳለች..ማለዳ የነፍሷ ውብ ስዕል ነው። በትናንት በዛሬዋና በነገዋ ውስጥ የተቀለመ። ራሷን ሙሉ ሆና የምታገኘው በአራስ ጀምበር ፊት ነው። ንጋት የሕይወቷ መጀመሪያና መጨረሻ ነው። ጀንበር ምሥራቅ አድማስ ላይ ስታቅላላ፣ ሰማይ በቀይና በጥቁር ሁለት መልክ ብርሃን ሲያሸበርቅ መኖር ደስ ይላታል። ምድር በአራስ ጀምበር ስትረሰርስ፣ ቀዬው የእንቁላል አስኳል ሲመስል ያኔ ሌላ ናት። ራሷን ፈልጋ የምታገኘው በዚህ እውነት ውስጥ ነው። በዚህ እውነት ውስጥ መኖር የምንጊዜም ምኞቷ ነው።

የነፍሷን ውብ ስዕል ንጋትን ሽታ ከነሌሊት ልብሷ ወደ መስኮቱ ተራመደች። መሬት የሚልስ ረጅም ልብሷን በእጇቿ አንቃ። ጸጉሯ ከሌሊት ልብሱ አፈንግጦ ጀርባዋ ላይ ይቦርቃል..እናቷን በሚያስታውሳት መልኩ ተጎንጉኖ። ጸጉሯ የእናቷ ማስታወሻ ነው...በወር አንድ ጊዜ አብረሃም እንደሚወደው ካልተሠራች በስተቀር ሁሌም ሹሩባ ነው። አብረሃም የልጅነት ፍቅረኛዋ ነው። አሁን የት እንዳለ አታውቅም። ድንገት ነው እንዲህ እንደ አሁኑ ማለዳን ሽታ በቆመችበት ወጥቶ የቀረው። በነፍሷ የሁለት ሰዎች ንብረት ናት.. የእናቷና የአብረሃም። እናቷ የአእምሮ ህመምተኛ ናቸው አማኑኤል ሆስፒታል ነው የሚገኙት። ሁሌ ጠዋትና ማታ ከሹሩባዋ ጋር እየሄደች እቅፋቸው ውስጥ ትወድቃለች። እስከ አስራ ስምንት አመቷ ድረስ ጸጉሯን የሚሠሯት እናቷ ነበሩ። ያንን ሁሉ ዘመን ከሹሩባ ሌላ ሠርተዋት አያውቁም። ከነሹሩባዋ እናቷ ፊት መቆም ደስ ይላታል..እናቷን ከህመም የሚያሽርላት ይመስላታል። ትናንትን የሚመልስላት ይመስላታል። አብረሃም በነፍሷ ላይ ሳይሞት የሚኖር ነፍስ ነው። ጠይም ነው..እንደ መስቀል ደመራ እንጨት ዘለግ ያለ። እንደ እናቷ የሳለችው በሕይወቷ ውስጥ ዳግም እንዲፈጠር የምትሻው አንድ እውነቷ ነው። ንጋትን ያስለመዳት..ማለዳን ያስወደዳት እሱ ነው። ሁሌ እንዲህ እንደ አሁኑ በሚነጋ ሰማይ ፊት እሷን አጠገቡ አድርጎ ‹እኔና አንቺ ጀምበርና ሰማይ አንድ ዓይነቶች ነን። አንዳችን ያላንዳችን ስፍራ የለንም። ሰማይ ለጀምበር መድመቂያዋ ነው። ጀምበር ለሰማይ ውበቱ ናት። እኔና አንቺም እንዲሁ ነን..እንደዚህ ንጋት ይላት ነበር።

ሊነጋ ያለን ሰማይ እንደማየት ደስታ የላትም። ከደመና ለመውጣት የምትተናነቅን ጀንበር እንደማየት ፍሰሀ የላትም። ብርሃን ከጨለማ ውስጥ ሲወጣን የመሰለ ድንቅ ተፈጥሮ አታውቅም። በብርሃን የተሳለን ድንቅ ተፈጥሮ ቆሞ እንደማየት ጥበብ አታውቅም። በጎጆአቸው ውስጥ ሆነው የሚያንሾካሹኩ ወፎችን እንደመስማት፣ በቤታቸው ውስጥ ሆነው ንጋት አብሳሪ አውራ ዶሮዎችን እንደማድመጥ ጥኡም ሙዚቃ አታውቅም። በጋጣቸው ውስጥ ሆነው፣ በጉሬአቸው ውስጥ ተደብቀው የሚቁነጠነጡ ነፍሳትን እንደመስማት ዓለም የላትም። ግን ብዙ ናፍቆት አለባት..ብዙ ትዝታ። በሕይወቷ ውስጥ እንዲመለሱ፣ ዳግም እንዲፈጠሩ የምትፈልጋቸው ትናንትናዎች አሉ። ትኖራቸው ይሆን? አታውቅም።

መስኮቱን ከፈተችው...እንዳሰበችው ሆነላት። ጠይም ምድር፣ ጠይም ሰማይ፣ ጠይም ተፈጥሮ ፊቷ ላይ ተጋረጠ። ብርሃንና ጨለማን የቀላቀለ ጅብማ ዓለም ተቀበላት። ደስ አላት..ሰማያዊ ደስታ። እንዲህ ደስ የሚላት ከዕለታት አንድ ቀን ነው እና እንዲህ እንደ አሁኑ ሊነጋ ባለ ሰማይ ስር ስትቆም። እንዲህ ደስ የሚላት በመኝታዋ ግርጌ ካለው የግራር ዛፍ ላይ ያሉ ወፎች ሲንጫጩ..የእማማ ስህን አውራ ዶሮ ሲጮህ.. እና እናቷ ፊት ስትቆም..አብረሃም ትዝ ሲላት።

ጎረምሳ ንፋስ አጠናፈራት። ደረቷን አላግቶ፣ የሌሊት ልብሷን አወናጭፎ ወደ ሳሎኗ ሲገባ አላስተዋለችውም ነበር። ወደ ሰማይ አየች.. ቀይ ጥቁር፣ ቡናማና አመዳማ የብርሃን ሽርጥ አሽርጧል። ወደ ምሥራቅ ቀና አለች.. ምሥራቅ አድማስ በብርሃን ለሀጭ ተዝረክርኳል። ልጃገረድ ኮረዳ ጀምበር ማርያም..ማርያም በሚሉ ወዳጆች ታጅባ ንጋትን ለመውለድ ስታምጥ ይታያታል። በዙሪያዋ ሽር ጉድ የሚሉ ጠይምና ቀይዳማ የብርሃን መልኮች ከበዋታል። የእግዜር እውነት ይገርማታል። በመኝታዋ ግርጌ ዋርካው ላይ የሰፈሩት አእዋፍት ማለዳን ሲያበስሩ ይገርማታል። የጎረቤታቸው የእማማ ስህን አውራ ዶሮ እኩለ ሌሊትን ለመነገር ነፍስ ማወቁ ይሄም ያስደንቃታል። የእግዜር እውነት ይገርማታል። በብርሃን ውስጥ ጨለማ፣ በጨለማ ውስጥ ብርሃን ማኖሩ፣ በትናንት ውስጥ ዛሬን..በዛሬ ውስጥ ነገ መደበቁ ያስደንቃታል።

ወደ ጀንበር አየች..ምጥ ላይ ናት..ብርሃንን ለመገላገል። እዬዬዋ ይሰማታል..ልጇን ወልዳ ለመሳም ያላት ጉጉትም። የሰው ልጅ ያልደረሰበት የተፈጥሮ እውነት ንጋት ውስጥ ያለ መሰላት። በመኖር ውስጥ ያለው ስውር እውነት መሽቶ መንጋት..ነግቶ መምሸት ነው ስትል አሰበች። በንጋት ስር መቆም፣ በንጋት ስር ተፈጥሮን መቃኘት ደስታዋ ባለፈ የእውነቷ መገኛ ስፍራ ነው። የጠፋባትን እውነት በንጋት ጉያ ውስጥ ነው የምታገኘው። እንዲመለሱ የምትሻቸውን ትናንትናዎች በመስኮቱ አሻግራ ሰማዩ እርቃን ላይ ነው የምታያቸው። ከቀይና ከጥቁሩ የብርሃን ኳል እያጠቀሰች ራሷን ሳለችው። እየነጋች..እየፈካች ራሷን አገኘችው።

ኮቴ ሰማች..

በንጋት ትካዜ ውስጥ ናት። የጀምበርን ምጥ እያማጠች..ጭንቀቷን እየተጨነቀች። በትካዜዋ ውስጥ ሳለች አንድ ሰው ውልብ አለባት...ከጨለማው ጋር የተመሳሰለ አንድ ሰው። እንደ መስቀል ደመራ ዘለግ ያለ።

ወደምትናፍቀው እውነት እየቀረበች እንደሆነ አላስተዋለችም። እምነቷን ከጀምበሯ መገላገል በኋላ ወዳለው አዲስ ዓለም አድርጋ ጠበቀች። እንደዛሬ የሆነ ንጋት ያየች አይመስላትም። በጀምበር ጉያ ውስጥ ይሄ ነው የማትለው የሆነ እውነት ይታያታል። ወደ እሷ የተዘረጋ እውነት..

በቆመችበት ምድር ወገገ አለች። ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ሰማይ ቀና አለች..ጀምበር ወልዳ..ምሥራቅ አድማስ በብርሃን አቅላልቶ አየች። የምትጠበቀው እውነት ይሄ ነበር። ልትደርስበት የምትሻው ሀቅ ይሄ ነበር...ሳቀች በነፍሷ።

ዕለተ ማክሰኞ ወገግ ሲል ከመስኮቱ ጋ ፈቀቅ አለች። ወደ እናቷ ጋ ልትሄድ ወደ ኋላዋ ስትዞርና በሩ ሲቆረቆር አንድ ሆነ።

በሩን ከፈተችው..

ያየችውን ማመን አልቻለችም..እንደ መስቀል ደመራ እንጨት ዘለግ ያለ አንድ ሰው በር ላይ ቆሟል። አብረሃም።

# ዓለም አቀፍ

## በአገሯ የሚሰለጥኑ የዩኬ ወታደሮች የመብት ጥሰት መፈጸማቸውን ተከትሎ ኬንያ ሕጓን አሻሻለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

በኬንያ የሚሰለጥኑ የዩናይትድ ኪንግደም ወታደሮች ከፍተኛ ጥሰቶች ፈጽመዋል መባሉን ተከትሎ አገሪቷ ከዩኬ ጋር ያላትን የመከላከያ ስምምነት ሕጓን አሻሻለች።

የኬንያ ፓርላማ ባሳለፈው አዲስ ማሻሻያ መሠረት የዩናይትድ ኪንግደም ወታደሮች በአገሪቱ ይከሰሳሉ።

የዩናይትድ ኪንግደም ወታደሮች ግድያን ጨምሮ ፈጽመዋል በተባሉት ከባድ ወንጀሎችም በኬንያ ሕግ መሠረት የሚዳኙ ይሆናል።

ይህ ማሻሻያ የወጣው በአውሮፓውያኑ 2012 የተገደለችው ኬንያዊት ወጣት ፍትህ አለመገኘቱ ከፍተኛ ጥያቄ ማጫሩን ተከትሎ ነው።

አግነስ ዋንጂሩ የተባለችው ኬንያዊት በአገሪቱ ከሚሰለጥኑ የዩናይትድ ኪንግደም ወታደሮች ጋር ከአንድ መጠጥ ቤት ስትወጣ አብራ ከታየች በኋላ ደብዛዋ ጠፍቷል።

የ21 ዓመቷ ወጣት ከሦስት ወራት በኋላ በአንድ ሆቴል ውሃ ማጠራቀሚያ ውስጥ አስከሬኗ ተገኝቷል። እስካሁን ድረስም በእርሷ ግድያ ላይ ተጠያቂ የሆነ አካልም ሆነ ለፍርድ የቀረበ የለም።

ሰንደይ ታይምስ በአውሮፓውያኑ 2021 የዩናይትድ ኪንግደም መከላከያ ሚኒስቴር ግድያውን ለመሸፋፈን እየሞከረ ነው በሚል መዘገቡን ተከትሎ ሚኒስቴሩ ከኬንያ ባለስልጣናት ጋር በምርመራው ላይ ትብብር



እያደረገ መሆኑን ገልጿል።

በያዝነው ሳምንት ረቡዕ ሚኒስቴሩ ይህንኑ መልዕክት የደገመው ሲሆን «የዚህ ምርመራ ባለ ስልጣን የኬንያ ፖሊስ ነው። የዩኬ መከላከያ ወንጀል ኮማንድም ከኬንያ ፖሊስ ጋር እየተባበረ ሲሆን ምርመራቸውንም በተገቢው ለመደገፍ እንሳተፋለን» ብሏል።

የምርመራውን ሂደትም ለመጠበቅ ተጨማሪ አስተያየትም እንደማይሰጥም ሚኒስቴሩ አክሏል።

ነገር ግን በዚህ ሳምንት ረቡዕ ኬንያ ያሳለፈችው የመከላከያ ስምምነት ማሻሻያ ወደ ኋላ ተመልሶ ተፈጻሚ አይሆንም ይህም ማለት የዋንጂሩ ግድያ የተያዘበት ሂደት ላይ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም።

የኬንያ ፓርላማ የመከላከያ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኔልሰን ኮይች ከቢቢሲ ፎከስ ኦን አፍሪካ ሬድዮ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ማሻሻያው እንደ ዋንጂሩ ዓይነት ግድያዎች እንደገና እንዳይፈጸሙ ያቆማል የሚል እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል።

ድንገት ግድያውም ከተከሰተ ወንጀለኞችንም ለመክሰስና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ማሻሻያው ይረዳል ብለዋል።

## ጋና ተስፋ የተጣለበትን የወባ ክትባት በማጽደቅ የመጀመሪያዋ አገር ሆነች

በጋዜጣው ሪፖርተር

በበለጸጉት ሳይንቲስቶች «ዓለምን ቀያሪ» የሚል ስያሜ የተሰጠውን የወባ ክትባት በማጽደቅ ጋና የመጀመሪያው አገር ሆናለች።

R21 በመባል የሚጠራው ክትባቱ ከዚህ ቀደም ከነበሩት ክትባቶች ጋር ሲነጻጸር በእጅጉ ውጤታማ ነው ተብሏል።

የክትባቱን ደህንነትና ውጤታማነት ሲፈትሽ የቆየው የጋና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ይፋ ባያደርገውም ጥቅም ላይ እንዲውል ውሳኔ አሳልፏል።

የዓለም ጤና ድርጅትም ክትባቱን ለማጽደቅ እያሰበ እንደሚገኝ ተሰምቷል።

በዓለም ዙሪያ ወባ በየዓመቱ 620 ሺህ ሰዎችን የሚገድል ሲሆን አብዛኞቹ ወጣቶች ናቸው።

ሰውነትን ከወባ አምጪ ተውሳክ የሚከላከለውን ይህንን ክትባት ለማበልጸግ አንድ ክፍለ ዘመንን የፈጀ ሰፊ ምርመራ ተደርጓል።

በቡርኪና ፋሶ በቅድመ ጥናት ወቅት በተደረገ ሙከራ R21ን ሦስት ጊዜ የወሰዱና በዓመቱ ማጠናከሪያ ክትባት የተሰጣቸው በሽታውን የመከላከል አቅማቸው 80 በመቶ አድጓል።

ሆኖም የክትባቱን ውጤት ማረጋገጫ ወደ 5 ሺህ የሚጠጉ ሕፃናት የሚሳተፉበት የሙከራ ክትባት የሚያስገኘው ውጤት ላይ የሚመረኮዝ ነው።

ይህንንም ባለፈው ዓመት መጨረሻ እንደሚደረግ ሲጠበቅ የነበረ ሲሆን ውጤቱ እስካሁን ይፋ አልሆነም።




ነገር ግን በአፍሪካ ለሚገኙ አንዳንድ ባለስልጣት እና ሳይንቲስቶች ደርሷል።

የሙከራውን ውጤት የተመለከተው የጋና ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ክትባቱ ከ5 ወር እስከ 3 ዓመት ያሉ ሕፃናት እንዲወስዱት ይሁንታ ሰጥቷል።

እንደ የዓለም ጤና ድርጅት ሁሉ ሌሎች የአፍሪካ አገራትም ክትባቱን ለማጽደቅ የቀረበላቸውን መረጃ እያጠኑ ነው።

አንድ በጋና የሚገኝ የሕንድ ተቋም በዓመት ከ100 እስከ 200 ሚሊዮን ክትባቶችን የሚያመርት ፋብሪካ በጋና ይገነባል።

አንዱ የ R21 ክትባት እስከ ሁለት ዶላር ሊሸጥ እንደሚችል ተገምቷል።

# ስፖርት





## የገረመው ደንቦባ መታሰቢያ የብስክሌት ውድድር ሊካሄድ ነው

አስማየሁ ግዛው

የአዲስ አበባ ብስክሌት ፌዴሬሽን ለቀድሞ ብስክሌተኛ ገረመው ደንቦባ የመታሰቢያ ውድድር ለማዘጋጀት ማቀዱን አስታወቀ። የመታሰቢያ ውድድሩ ከክለቦች ቻምፒዮና ጎን ለጎን በመጪው ወር የመጀመሪያ ሳምንት እንደሚካሄድ ታውቋል።

ብስክሌት በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ካላቸው ስፖርቶች መካከል አንዱ ሲሆን፤ አንጋፋው ብስክሌተኛ ገረመው ደንቦባ ደግሞ ከፈር ቀዳጆቹ ጋላቢዎች መካከል አንዱ ናቸው። በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት አንጋፋው ብስክሌተኛ ገረመው ደንቦባ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በተካፈለችበት የሜልቦርን ኦሊምፒክ (እ.አ.አ 1956) ሀገራቸውን ወክለው ጠንካራ ተፎካካሪ በመሆን አስደናቂ ታሪክ የሰሩ ስፖርተኛ ናቸው። በተወዳዳሪነት ዘመናቸው በግል ባደረጓቸው ውድድሮች በርካታ ሜዳሊያዎችን በማግኘት ለሀገራቸው ብስክሌተኞች አርዓያ መሆን ችለዋል።

በጎዳና ላይ በተደረገ የዓለም የብስክሌት ግልቢያ ውድድር 24ኛ ደረጃን ይዘው ያጠናቀቁ ሲሆን ያስመዘገበው ደረጃ ከአፍሪካ እና ከእስያ ተፎካካሪዎቹ ቀዳሚ አድርጎታል። በጊዜው ኢትዮጵያ በብስክሌት በቡድን አራተኛ እንድትወጣም አስችለዋል። 17ኛው የኦሊምፒክ ጨዋታዎች በጣሊያን ሮም እ.ኤ.አ በ1960



በቅርቡ ሕይወቱ ያለፈው አንጋፋው ብስክሌተኛ ገረመው ደንቦባ፤

ሲካሄድ ገረመው የተካፈሉ ሲሆን አሰልጣኝነት እ.ኤ.አ በ1968 ጃፓን ባዘጋጀችው 19ኛው የኦሊምፒክ ጨዋታዎች የተካፈለውን ቡድን በአሰልጣኝነት መርተዋል።

ከተወዳዳሪነት ባለፈ የኢትዮጵያ ብስክሌት ብሄራዊ ቡድንን ለበርካታ ዓመታት ማሰልጠን የቻሉትን አንጋፋውን የሀገር ባለውለታ ለመዘከርም ከመታሰቢያ የብስክሌት ውድድሩ በተጨማሪ ሻማ የማብራት መርሀ ግብር እንደሚያዘጋጅም የአዲስ አበባ ብስክሌት ፌዴሬሽን አስታውቋል።

የመታሰቢያ ውድድሩ በመጪው ግንቦት 6/2015 ዓ.ም እንደሚካሄድ የተጠቆመ ሲሆን፣ ይህም የቀድሞውን ታሪካዊ ብስክሌተኛ በመዘከርና የሰራቸውን ጀብዶች ለትውልድ አርዓያ እንዲሆን የማድረግ አላማ ያለው ነው።

የብስክሌት ስፖርት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መቀዛቀዝ ቢታይበትም መሰል ውድድሮችን በማዘጋጀት ለማነቃቃት እየተሞከረም ነው። ከዚህ መታሰቢያ ውድድር በተጨማሪ የአዲስ አበባ ክለቦች ቻምፒዮናም ይካሄዳል። በእነዚህ ውድድሮች በሚደረገው ፉክክር ሀገርን የሚወክሉ ብስክሌተኞችን በማስመረጥ በዓለምና አህጉር አቀፍ ውድድሮች እንዲሳተፉም ይደረጋል።

ሀገር ውስጥ ከሚደረጉት የብስክሌት ውድድሮች መካከል የክለቦች ብስክሌት ቻምፒዮና አንዱ ሲሆን፤ በአዲስ አበባ ብስክሌት ፌዴሬሽን አዘጋጅነት የ2015 ዓም የክለቦች ቻምፒዮና ካለፈው መጋቢት 17/2015 ዓ.ም ጀምሮ እየተካሄደ ይገኛል። ውድድሩ መነሻውንና መድረሻውን ቴዎድሮስ አደባባይ በማድረግ መጀመሩም ይታወሳል።

ውድድሩ በተለያዩ ደረጃዎች በርካታ ፉክክሮችን እያስተናገደ ባለፉት ሶስት እሁዶች ተካሂዷል። ውድድሩ በሳምንቱ መጨረሻ በእረፍት ቀናት የሚደረግና ለበርካታ ሳምንታት የሚቀጥል በመሆኑም ለስፖርተኛውና ለስፖርት ቤተሰቡ ጥሩ አጋጣሚን እንደሚፈጥር ይጠበቃል። የቻምፒዮናው ሁለተኛ ሳምንት ውድድሮች ሚያዝያ 1 ቀን/2015 ዓ.ም ከወሎ ሰፈር ወደ ኡራኤል በሚወስደው ጎዳና ሲካሄድ በክለቦች፣ በግል ተወዳዳሪዎችና ታዳጊዎች መካከል ተስፋ ሰጪና ጥሩ ፉክክር ታይቶ አሸናፊዎች ተለይተዋል።

ፌዴሬሽኑ በየዓመቱ የሚያዘጋጀው ይህ የክለቦች ቻምፒዮና ክለቦች፣ ታዳጊዎች፣ የግል ተወዳዳሪዎችና የቀድሞ ብስክሌተኞች የሚሳተፉበት ውድድር ነው። ቻምፒዮናው ከተወሰኑ ሳምንታት እረፍት በኋላ ሚያዚያ 22/2015 ዓ.ም ቀጥሎ የሚካሄድም ይሆናል። የቀሩትን አምስት ዙሮች ጨምሮ እስከ ግንቦት 20/2015 ዓ.ም ድረስም የተለያዩ ፉክክሮችን በማስተናገድ ፍጻሜውን የሚያገኝ ይሆናል።

በተለያዩ ዙሮች በሚካሄደው በዚህ ቻምፒዮና የመብራት ኃይል፣ ፌዴራል ፖሊስ፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚና ጋራድ ተሳታፊ እንደሆኑም ለማወቅ ተችሏል።

የአዲስ አበባ ብስክሌት ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ረዘነ በየነ፤ ስለውድድሩ ዝርዝር ጉዳዮች ወደ ፊት እንደሚገለፅ ጠቁመው፤ እነዚህ ውድድሮች ከዚህ ቀደም ይካሄዱ የነበሩ ረጃጅም የብስክሌት ውድድሮች በጸጥታ ጉዳይ በመቅረታቸው የከተማ ውስጥ የዙር ውድድሮችን ማድረግ እንደ መፍትሔ መወሰዱን አክለዋል።


### ለሁለተኛ ጊዜ የወጣ ሀገር አቀፍ ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ
### መለያ ቁጥር GGWW/008/2015

በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት በጉራጌ ዞን በገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤት በ2015 ዓ.ም በጀት አመት ለገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ ውሀና ማእድን ኢነርጂ ፅ/ቤት በመደበኛ በጀት የሞተር ፓምፕና ጄኔሬተር በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

**ስለሆነም ተጫራቾች**

1. የዘመኑን ንግድ ፍቃድ ያሳደሱ የቫት እና ቲን ነምበር ተመዝጋቢ መሆናቸውን የሚገልፅ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን አለባቸው፡፡
2. በጨረታው ለመወዳዳር የሚፈልጉ ተወዳዳሪዎች የሚገዙት ጨረታ ሰነዱን ጠቅሰው በማመልከቻ ሲጠይቁ ተወካዮች ከሆኑ ከድርጅቱ ህጋዊ ውክልና ይዘው መምጣት አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15ኛው ተከታታይ ቀናት እስከ 8፡00 ሰአት ድረስ የማይመለስ ብር 50 /ሃምሳ ብር ብቻ በመክፈል የጨረታውን ሰነድ መሀል አምባ ገደባኖ ጉታር ወለኔ ወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 03 ድረስ በመቅረብ መውሰድ ይችላሉ።
4. የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ብር 10000(አስር ሺህ ብር) በገ/ጉ/ወ/ወ/ፋይናንስ ጽ/ቤት ስም ማሰራት አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች የጨረታውን ቴክኒካል እና ፋይናንሻል ዶክመንት ሀ/ ለቴክኒካል ዶክመንት አንድ ኦርጅናል እና ሁለት ፎቶ ኮፒ በማድረግ ቴክኒካል በሚል በመለየት ለ/ለፋይናንሻል ዶክመንት አንድ ኦርጅናል እና ሁለት ፎቶ ኮፒ በማድረግ ፋይናንሻል በሚል በመለየት በሰም በማሸግ ከላይ በተጠቀሰው የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ/ከባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ከፋይናንሻል ኦርጅናል ዶክመንቱ ጋር በማድረግ በማሸግ ፋይናንሻል ዶክመንት በሚል በመለየት ይህ ማስታወቂያ አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15(አስራ አምስት ) ተከታታይ ቀናት መሀል አምባ የገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 03 ድረስ በመምጣት ለጨረታ አገልግሎት በተዘጋጀው ሳጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
6. የጨረታው ሰነድ በ15ኛው ተከታታይ ቀን ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ይታሸጋል ከቀኑ 8፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
7. መስሪያ ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
8. ጨረታው የሚከፈትበት ቀን በአል ወይም ቅዳሜና እሁድ ከሆነ ወደ ሚቀጥለው የሥራ ቀን ይዘዋወራል፡፡
9. በግዢ ኤጀንሲ በእቃ አቅርቦት ምክንያት ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ድርጅቶች መወዳደር አይችሉም።

**ለበለጠ መረጃ፡-** ስልክ ቁጥር 0113360631/0113360146 ይደውሉ

**ገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤት**



### ለሥራ ፈላጊዎች የወጣ ማስታወቂያ

በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ በሚከተሉት ክፍት የሥራ ቦተዎች አመልካቾችን አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ብዛት | የትምህርት ዓይነት | የትምህርት ደረጃ | የሥራ ልምድ | ደረጃ | ደመወዝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሙያ ደህንነትና አካባቢ ጥበቃ ባለሙያ | 2 | በሙያ ደህንነት ወይም አካባቢ ጥበቃ | ቢ.ኤ | 2 ዓመት | XI | 7.101.00 |
| 2 | ከፍተኛ የአውቶብስ ሾፌር | 1 | ህዝብ 2/ተመጣጣኝ ደረጃ መንጃ ፈቃድ | 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ | 4 ዓመት | IX | 4,409.00 |
| 3 | ኒሲየር ኤሌክትሪሽያን | 1 | ኤ/ኤሌክትሮኒክስ | ሌቭል 4 | 4 ዓመት | XI | 7,101.00 |
| 4 | ሲኒየር ኢንስትሩመንት ቴክኒሽያን | 1 | ኤ/ኤሌክትሮኒክስ | ሌቭል 4 | 4 ዓመት | XI | 7,101.00 |
| 5 | ኢንስትሩመንት ቴክኒሽያን | 1 | ኤ/ኤሌክትሮኒክስ ኢንጂነሪንግ | ሌቭል 4/3 | 0፣2 ዓመት | IX | 4,409.00 |
| 6 | ሲኒየር የኮሮዥን ሮቴክሽንና ላይኒንግ ቴክኒሽያን | 1 | ብሪክስ ላይኒንግ /ፕላስተሪንግ/ ግንብ ሥራ | ሌቭል 4 | 4 ዓመት | XI | 7,101.00 |
| 7 | ጁኒየር ኢንሱሌሽን መካኒካል | 1 | ጀኔራል መካኒክስ | ሌቭል 3/2 | 0፣2ዓመት | VIII | 3,644.00 |
| 8 | ሲኒየር አውቶ መካኒክ | 2 | በአውቶመካሊክስ | ሌቭል 4 | 4 ዓመት | XI | 7,101.00 |
| 9 | አውቶ ኤሌክትሪሽያን | 1 | አውቶ ኤሌክትሪሽያን | ሌቭል 4/3 | 0፣ 2 ዓመት | IX | 4,409.00 |
| 10 | ሲኒየር ማሽኒስት | 1 | ጀነራል ሜካኒክስ | ሌቭል 4 | | XI | 7,101.00 |
| 11 | ማሽኒስት | 1 | ጀነራል ሜካኒክስ | ሌቭል 4/3 | | IX | 4,409.00 |

በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ ከላይ የተጠቀሰውን መስፈርት የምታሟሉ አመልካቾች በ15 /አሥራ አምስት/ ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ አዋሽ መልካሳ የሰው ሀብት አመራር ቢሮ ቁጥር 17 እየቀረባችሁ ማመልከት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

በሌቭል የትምህርት ደረጃዎች የብቃት ማረጋገጫ /COC/ማቅረብ ይኖርባችኋል፡፡

**ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር፡-251 222 225 0247መጠየቅ ትችላላችሁ**

**በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ**